# ኤዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት

## ሞጁል ሶስት

# የልጆች ቋንቋ መዳበር
# Language Development in (Pre-School) Children



## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

ጥቅምት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ESD

# ኤዱኬሽን ፎር ሰስቴነብል ዲቨሎፕመንት

# ልጆች ቋንቋ መዳበር

# (Language Development)

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

**አማካሪ ፡** ፍሮምሲስ የትምህርትና ስልጠና ኢ.ማ

**አዘጋጅ ፡** ደመወዝ አድማሱ

## ማውጫ


ምስጋና ........ ii

መቅድም ........ iii

የስልጠናው ቢጋር / outline/........ vi

1. ቋንቋ ........ 1

እንደመግቢያ........ 1

1.1 ትርጉም ፣ዓላማ ፣ ፅንሰ ሃሳቦች ........ 3

*1.2 የቋንቋ መዳበር በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ*........ 6

1.3 የቋንቋ ግብዓቶችና ተከታታይነት ያለው ግንኙነት........ 8

1.4 ወላጆችና የህፃናት ቋንቋ መዳበር ........ 11

*1.5 ቤተሰብ፣ ባህልና ቋንቋ* ........ 12

1.6 የቋንቋ መዳበርና የሪሶርስ እጥረት........ 14

1.7 ህፃናትን ለትምህርት ቤት ማዘጋጀት ........ 16

1.8 ቋንቋና የህፃናት ጨዋታ ........ 18

1.9. የንባብ ዝግጁነት ቋንቋ የሚያጫውተው ሚና........ 19

1.10 ቋንቋና ማህበራዊ ተግባቦት ........ 20

1.11 ቋንቋና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ........ 22

1.12 የምዕራፉ ማጠቃለያ ........ 23

2. በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የቋንቋ ዝግጁነትን እንዴት ማምጣት እንችላለን? ........ 26

የቋንቋ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 48

ዋቤ መፅሐፍት ........ 52

አባሪ 1: Basic Facts about Language........ 53

አባሪ 2: አካባቢያዊ ግንዛቤ........ 54

አባሪ 3፡ የምእራፍ አንድ የሙከራ ጥያቄዎች መልስ ........ 55

አባሪ 4፡ የምእራፍ ሁለት የሙከራ ጥያቄዎች መልስ ........ 56

አባሪ 5፡ የእንቆቅልሽ መልስ........ 57

# ምስጋና

ይህ ሞጁል የተዘጋጀዉ በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ እና በኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ትብብር ሲሆን ለዚህም  ማህበሩ ለኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡ በተለይም በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ ስር ሆነዉ በሞጁል ዝግጅትና በስልጠ በየሞያ ዘርፋቸዉ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ባለሙያዎች ከልብ ያመሰግናል ፡፡

በመጨረሻም የኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ሰራተኛች ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማስተካከል ስልጠናዉ የተሳካ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋፅኦ ማህበሩ  ምስጋናዉን ያቀራባል፡፡

# መቅድም

ውድ መምህራን ፣ የዚህ ሥልጠና ተካፋዮች እድሜያቸው ለመደበኛ ትምህርት ካልደረሱ ልጆች ጋር በመሥራት ላይ ናችሁ ወይም ለመስራት የተዘጋጃችሁ ናችሁ፡፡ እነዚህን ልጆች ወይም ህፃናት ለመደበኛ ትምህርት በማዘጋጀት ላይ ትገኛላችሁ ፡፡ እነዚህን ልጆች በመርዳት በመደበኛው የትምህርት ደረጃ ለሚገጥማቸው የመማር ተግባር ማለትም ሂሳብን /ስሌት ፣ ንባብን ፣መፃፍን፣መዝሙርን፣ ሥዕልን ወዘተ ለመማር ታዘጋጃላችሁ ፡፡ በመሆኑም ይህ የእናንተ የሥራ ምትክ የሌለውና ለህፃናቱ መሠረት የሚጥል ነው ፡፡ ህጻናት በተስተካከለ መሰረት ላይ መደበኛውን ትምህርት ከጀመሩ ደግሞ በህይወታቸው ስኬታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ይህን መሠረት ለመጣል፣ቀጣይ የተሰተካከለ የትምህርትና የሕይወት ጉዞ ለመጀመርና በውጤት ለማጠናቀቅ ደግሞ ዋናውና ቁልፍ የመግባቢያ መሣሪያ የሆነው ቋንቋ ነው ፡፡ በመሆኑም በዚህ ሞጁል የምናተኩረው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ወላጆች፣አሳዳጊዎች ፣ቤተሰብ ፣ ማህረሰቡና በተለይም እናንተ መምህራን ህጻናቱ/ልጆቹ ቋንቋ የሚያዳብሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ላይ ነው ፡፡ ለዚህም ይረዳን ዘንድ ተሞክሯችንን /ልምዳችንን ከማንጸባረቃችን በተጨማሪ ጥናታዊ ፅሁፎችን እንመለከታለን ፡፡ ከአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔ ጋር ለማዋሀድም ጥረት እናደርጋለን ፡፡

ምንም እንኳ የሌሎች የህብረተሰቡ አባላትን ድጋፍና እገዛ የምንመለከት ቢሆንም ዋናው ትኩረታችን ግን እኛ መምህራን ለህፃናቱ ቋንቋ መዳበር የምንከተላቸው ዘዴዎች ላይ ይሆናል፡፡ ውይይታችንና ሥልጠናችንም የጥናትና ምርምር ዕውቀቶችንና ግኝቶችን እንዳለ መውሰድ ላይ ያትኮረ ሳይሆን ከአካባቢያችን ሁኔታና የተካበተ ዕውቀት ጋር የማዋሀድን ዘዴ በመጠቀም ይሆናል፡፡

ሥልጠናውን ፍሬያማ ለማድረግም አምስት ነገሮች ግምት ውስጥ ገብተዋል፡፡

1. የማሰልጠኛ ማቴሪያሉ ሲዘጋጅ የሠልጣኞችንና የአሠልጣኞችን ዕውቀት፣ ልምድና ተሞክሮ ለማካተት ተሞክሮአል፡፡ ይህን ስንል የራሳችን የህይወት ማለትም የቋንቋ መዳበር ተሞክሮ፣ የታናናሽ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የቋንቋ አስተምሮህት፣ የልጆቻችን የቋንቋ አስተምህሮ ተሞክሮ በአጠቃላይም የቋንቋ መዳበር ሂደትና መስተጋብርን መሠረት አድርጓል፡፡

2. በሳይንሳዊ መንገድ ተጠንቶ የተገኘና የተቀናበረ ዕውቀትን አካቷል፡፡ በዋነኛነት የተባበሩት መንግስታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ የህፃናት ቋንቋ ማዳበርን አስመልክቶ የሚጠቅምበትን የሥልጠና ማኑዋል መሠረት አድርጓል፡፡
3. ይህ የሥልጠና ማኑዋል ተማሪ /በዚህ ልዩ ሁኔታ ሰልጣኝ/ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል ፡፡ ይህም ማለት አሰልጣኙ ዕውቀት ሰጭ፣ ሰልጣኞች እውቀት ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ ሁለቱም ወገኖች ሠልጣኞችም ሆኑ አሰልጣኞች ያካበቱትን ልምድና ዕውቀት የሚጋሩበት እንዲሆን ለውይይት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡
4. አብዛኛው ሳይንሳዊና የምርምርና ፅሁፍ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ የተወሰደ በመሆኑ ውይይታችን በአማርኛ ቢሆንም እንደ አስፈላጊነቱ እንግሊዝኛን እንጠቀማለን፡፡ እናንተም ሁለቱንም ቋንቋዎች መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ቋንቋ ለመማር ቋንቋውን መጠቀም (practice) ቁልፍ ጉዳይ ስለሆነ እንግሊዝኛውን መጠቀም ስትፈልጉ ስለ ስህተቱ ቀድማችሁ አትጨነቁ፡፡ ቋንቋን የምንማረው ስንጠቀምበት ነው ፡፡ በዚህ ሂደት ስህተታችንን እያረምን ቋንቋችንን እያዳበርን እንሄዳለንና፡፡ በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት ያለው ሂደት ይኼው ነው ፡፡
5. በዚህ ፅሁፍና በአጠቃላይም የስልጠናችን ሂደት መሠረታዊ የቋንቋ ትርጉም ፣ ባህሪያትና ክህሎቶችን ከተመለከትን በኋላ ጠቃሚ የቋንቋ ማዳበሪያ ወይም ማስተማሪያ ዘዴዎች እናጠናለን ፣ እንለማመዳለንም ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች/የሞጁሉ ተጠቃሚዎች**

*ሥልጠውና ግቡን መምታቱን/ ውጤታማ መሆኑን ማወቅ እንችላለን? መልሳችን “አዎ” ከሆነ እንዴት?*

የዚህ ጥያቄ መልስ በእርግጥም “አዎ” ነው፡፡ ምክንያቱም ዓላማችን ግቡን መምታቱን ብቻ ሳይሆን መጠኑንም ጭምር ማወቅ ይቻላል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም ይዘቱን ምን ያህል እንደተገነዘብነው ለማረጋገጥ ጥያቄና መልስ ይኖረናል፡፡ የእናንተ ተሳትፎ ለዚህ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ይሆናል፡፡ ቀጥተኛ ማለትም እንደ ሙከራ፣ ፈተና እና ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ውይይቶችን ጥያቄና ምላሾችን፣ የግልና የጋራ /ቡድን ሥራዎችን ፣ ሪፖርቶችን ፣ ገለፃዎችን ፣ ግብረ መልሶችን ወዘተ... የመሳሰሉትን እንጠቀማለን፡፡ 90% በላይ በዚህ ሥልጠና መሳተፍም እንደጠቋሚ እናየዋለን ፡፡

ለመነሻ ያህል ይህን ይህን ያህል ካልን ፣የሥልጠናው ይዘትና አደረጃጀት ላይ ያላችሁን አስተያየት ትሰጡኛላችሁ ፡፡ የምትሰጡት አስተያየት በሰልጠናው ሊካተቱ የሚገባቸው ይዘቶች ካሉ ለማካተት ይረዳናል፡፡ በተጨማሪም ውይይታችን የእናንተን ፍላጎትና ችግሮች /ክፍተት/ መሠረት እንዲያደርግ ይረዳናል፡፡

የእናንተ ከቋንቋ መዳበር ጋር የተያያዘ ተሞክሮ እና ገጠመኝ (ችግርም ቢሆን) የሥልጠናችን ማጣፈጫ ቅመም ነውና ሥልጠናችንን አሳታፊ ለማድረግ እንጣር! ተረቶች፣ ገጠመኞች፣ቀልዶችና እንቆቅልሾች የቋንቋ መማሪያ ዘዴዎች ከመሆናቸውም በላይ ማነቃቂያ ይሆናሉ፡፡ ይህ ሲሆን ነው ሥልጠናው ትርጉም የሚኖረው፤ እናንተም የምትወዱትና በንቃት የምትሳተፉት፡፡

በመጨረሻም እኔም እንደ እናንተ መምህር ነኝ፤ በአንድ ሙያ ያለንና ለተመሳሳይ ዓላማ የተሰለፍን ባለሙያዎች ነን ፡፡ ስለዚህ ያካበትነውን ልምድ እንካፈላለን ፡፡ የሰጭና የተቀባይ መንፈስ ሳይሆን የመማማር መንፈስ ይዘን እንቀጥላለን፡፡

አመሰግናለሁ።

**የስልጠናው ቢጋር / outline/**

የሥልጠናው ርዕስ  ፡- የልጆች ቋንቋ መዳበር

የሚወስደው ጊዜ ፡-  6 ሌክቸር ሰዓት

***የስልጠናው ዓላማ***

**ሠልጣኞች ሥልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦችን ይረዳሉ፣
- የቋንቋ መዳበርን የሚወስኑ ነገሮችን ይገነዘባሉ፣
- ጨዋታ ለቋንቋ መዳበር የሚጫወተውን ሚና ያደንቃሉ፣
- አራቱን የቋንቋ ክህሎች ይለያሉ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቋንቋን ለማዳበር የሚጠቅሙ ዘዴዎችን ይለያሉ፣ ይተገብራሉ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የቋንቋ መዳበርን ይከታተላሉ፤ ይለካሉ፡፡

***የስልጠናው የትኩረት ነጥቦች***

- የቋንቋ መዳበር
- ጨዋታና ቋንቋ በቅድመ መደበኛ ትምህርት
- የቋንቋ ክህሎችን ማዳበር
- ቋንቋና ትምህርት
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የቋንቋ ማዳበሪያ ዘዴዎች
- ቋንቋን በቅድመ መደበኛ ትምህርት ለማዳበር የሚጠቅሙ ማቴሪያሎች

***የስልጠናው አተገባበር/ ዘዴ***

- መግቢያ
- ጥያቄና መልስ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ
- ሪፖርት ማቅረብ
- ተሞክሮን ማካፈል
- ፕሮጀክቶች
- አቀራረብ /ገለፃ

- ግብረ መልስ
- ማጠቃለያ

**የሥልጠናው ቋንቋ**

- አማርኛ
- እንግሊዝኛ / እንደአስፈላጊነቱ/

***የምዘና ዘዴ***

- የክፍል ውስጥ ተሳትፎ
- የጋራ ሥራ
- የግል ሥራ
- የፕሮጀክት ሥራ
- ፓርትፎሊዮ
- ጥያቄና መልስ
- ገጠመኞችን መገምገምና መተንተን
- ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች
- የፕራክቲከም የጽሁፍ ሪፖርት
- የፕራክቲከም አቀራረብና
- ሌሎችም እንደአስፈላጊነታቸው /ተመርጠው/ ተግባራዊ ይሆናሉ።

## 1. ቋንቋ

**እንደመግቢያ**

በዚህ ርዕስ ስር የቋንቋን ትርጉም ፣ ዓላማና ፅንስ ሃሳብ አስቀድመን እንመለከታለን፡፡ በመቀጠልም ቋንቋን ለማዳበር በቤተሰብና በአካባቢ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት፣ ቋንቋ ከጨዋታና ከሌሎች መሠረታዊ ዕውቀት ትምህርቶች ጋር ያለውን ግንኙነት እናያለን።፡፡

**ውድ ሰልጣኞች/የሞጁሉ ተጠቃሚዎች**

በዚህ ርዕስ ስር ልንመለከተው ይገባል የምትሉት የቀረ ነገር ካለ ጥቀሱ፡፡

________________________________________________

________________________________________________

______________________________

ወደ ዝርዝር ርዕሳች ከማለፋችን በፊት ለዚህ ሥልጠናም እንዲያግዘን በአንድ ሙያ ጥላ ስር ያለን በመሆናችንም ራሳችንን እናስተዋውቅ ፡፡ በዚህ ትውውቅ ጊዜ የምንጠቅሰው ሙሉ ስማችንን ፣ የተማርንበትን ትምህርት ቤት ፣ ከማስተማርና ልጆችን ቱቶር በማድረግ ያለንን ተሞክሮ ፣ የምንጠቀምባቸውን ቋንቋዎች፣ የወደፊት እቅዳችንና ራዕያችንን ፣ እንዲሁም ከዚህ ሥልጠና የምንጠብቀውን ውጤት ይሆናል፡፡ ራሳችንን ለማስተዋወቅ አማርኛም እንግሊዘኛም ልንጠቀም እንችላለን ፡፡ ሌላ የምትጨምሩት ነገር አለ?

________________________________________________

________________________________________________

_________________________________________

“ማን ይጀምር”? የሚለውን ጥያቄ እኔ እመልሰዋለሁ፡፡ ስሜ ደመወዝ አድማሱ ይባላል፡፡ የትምህርት ደረጃዬ ኤም ኤ ዲግሪ በትምህርት ሳይኮሎጂ ነው ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአዲ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርት በመከታተል ላይ እገኛለሁ ፡፡ 25 ዓመት የሥራ ልምድ አለኝ ፡፡ ይኸውም በአሰልጣኝነት ፣ በመምህርነት፣ በማህበራዊ ሠራተኛነት ፣ በተመራማሪነት ነው ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እሠራለሁ፡፡ ባለትዳርና የሁለት

ልጆች (ወንድና ሴት) አባት ነኝ፡፡ ከእናንተ ጋር ለስድስት ሰዓት በአሰልጣኝነት እቆያለሁ፡፡ ከእናንተ ጋር በመተዋወቁና በመቆየቴ ደስተኛ ነኝ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

አሁን የእናንተ ተራ ነው ፡፡ ማን ይቀጥል? ፈቃደኛ ካለ? ከሌለ አንድ ከፊት አንድ ከኋላ እያልን እንሄዳለን፡፡ አመሰግናለሁ ፡፡

ቀጥል/ይ

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________

ወደሚቀጥለው ጉዳይ ከመሸጋገራችን በፊት አንድ እንቆቅልሽ አለችኝ።

እንቆቅልሽ

ምን አውቅልህ አትሉም?

እሽ

እግር የላትም ትሮጣለች፤

አፍ የላትም ትናገራለች፤እወቁልኝ?

ማስታወሻ፡ የእንቆቅልሽ ስርዓቱን መከተል አትርሱ
የተለያዩ ጥያቄዎችንም በመጠቀም ቋንቋቸውንና የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ለማስፋት ሞክሩ፤፤ ምሳሌ፡ እግር ያለው ምኑን ነው? ሂደ ያለው ምኑን ነው? ወዘተ.

መልሱን በአባሪ 5 ተመልከቱ።

በድጋሚ አመሰግናሁ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች**

ይህ የስልጠና ሞጁል ከመዘጋጀቱ በፊት የእናንተን የሰልጣኞችን ፍላጎት ማጥናት ተገቢ ቢሆንም ይህ ተግባር አልተከናወነም። ስለዚህ የሌሎች ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን ልምድና የራሴን የረዥም ጊዜ የአሰልጣኝነት ልምድና ሙያ፣ ያነበብኩዋቸውን ፅሁፎችና ጥናቶች እንዲሁም ልጆቼን ሳሳድግ ያገኘሁትን የልምድ ዕውቀት መሠረት በማድረግ ይህን ፅሁፍ አዘጋጅቻለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ፅሁፍ ለሙከራ የቀረበና ያላለቀለት ስለሆነ በእናንተ አስተያየት የሚዳብርና የሚስተካከል ይሆናል፡፡ የእናንተ የተካበተ ልምድም የሚታከልበት ይሆናል፡፡

ደግሜ ለማስታወስ ስልጠናችን የውይይት ዘዴን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ጥያቄ ወይም አስተያየት ሲኖራችሁ አትለፉ። እናንተም ስታስተምሩ በዚሁ መልክ ብታደርጉት የተማሪዎቻችሁን ትኩረት ታገኛላችሁ፣ የሀጻናትንም ፍላጎት ማርካት ትችላላችሁ። ይህ ተከናወነ ማለት ደግሞ ውጤታማ ሆናችሁ ማለት ነው። በመሆኑም በዚች አጭር የስልጠና ወቅት ተግባራዊ እናደርጋታለን፡፡

## 1.1. ትርጉም ፣ዓላማ ፣ ፅንሰ ሃሳቦች

**የንዑስ ትምህርቱ ዓላማ/ግብ**

የዚህ ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የቋንቋን ትምህርት ትርጉም ይረዳሉ።:
- የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ይዘረዝራሉ።
- የቋንቋን ጽንሰ ሀሳብ ያብራራሉ።
- ለቋንቋ መዳበር ወሳኝ የሆነውን ጊዜ ያሳያሉ።

**ውድ ሰልጣኞች**

ውይይታችንን በቋንቋ ትርጉም እንጀምራለን፡፡ የቋንቋን ትርጉም ፃፉ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________

ቋንቋ በተናጋሪው ህብረተሰብ የሚታወቅና ሥርዓት ያለው የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በውስጡም ድምጾችን ፣ ቃላትን ፣ዓረፍተ ነገሮችን /ትርጉም ባላቸው አሰካክ/ ይይዛል፡፡ የምትጨምሩት ካለ ግለጹ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________

ቋንቋ አንድ ህብረተሰብ (እንሰሳትን አይመለከትም) ዕውቀቱን፣ ልምዱን ፣ ተሞክሮውን ፣ ሃሳቡን የሚለዋወጥበት መሳሪያው ነው ፡፡ ቋንቋ አካባቢያችንን ራሳችን የምንረዳበትና የምንገልፅበት መሳሪያ ነው፡፡

አንድ ጥያቄ ላንሳ ፡- ቋንቋ ለሰዎች ብቻ የተሰጠ መሳሪያ ነው ካልን እንስሳትስ የሚግባቡበት ቋንቋ የላቸውም ? እንዴት ? እስኪ ተወያዩበት።

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ሰዎች ቋንቋን እንዴት ሊማሩ ቻሉ የሚለው ይሆናል፡፡ እስኪ ተወያዩበት ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_____________________________________________________

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ባለሙያዎች የሚከራከሩባቸውን ጥያቄዎች እንመልከት፡፡ ከሌሎች ባለሙያዎች ቋንቋ በተፈጥሮ/ በውርስ የሚገኝ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በትምህርት / ከህብረተሰቡ የሚገኝ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡

የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች የሰው ልጅ ከሌሎች እንሰሳት በተለየ ቋንቋን ለመማር የሚያስችሉ አካላዊ ተፈጥሮዎች (ጉሮሮ ፣ ትናጋ፣ ዐዕምሮ ወዘተ) አሉት፡፡ እነዚህ አካላዊ ተፈጥሮዎችም በውርስ የሚያገኛቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ናቸው ቋንቋን እንዲጠቀም ያበቁት ብለው ይከራከራሉ። በሌላው ወገን የሰው ልጅ እንደ "ነጭ ወረቀት" ሊፃፍበት የሚችል /ባዶ ሲዲ ብሎ እንደማሰብ/ የሚችል ጭንቅላት ይዞ የተፈጠረ ነው ፡፡ በዚህ "ወረቀት" ላይ ህብረተሰቡ ቋንቋውን ይፅፍበታል ብለው ይከራከራሉ፡፡

እናንተ የትኛውን ወገን ትደግፋላችሁ?ለምን? ለአምስት ደቂቃ ተወያዩበት፡፡ ምሳሌዎችንም ጥቀሱ ________________________________________

________________________________________

____________________________

____________________________

በአሁኑ ጊዜ ያሉ ጥናቶች ያረጋገጡት ቋንቋ የሁለቱም ማለትም የውርስና የአካባቢ (heredity and environment )ድምር ውጤት መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት ሰው ለቋንቋ መፈጠርና መዳበር አስፈላጊ የሆኑ የሰውነት ክፍሎችን በውርስ ያገኛል፡፡ እነዚህ በውርስ ያገኛቸውን ለቋንቋ መፈጠርና መዳበር አስፈላጊ የሆኑ የሰው አካሎች ግን ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት ቋንቋውን ከህብረተሰቡ መማር ሲችል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ድምፁን፣ ቃላትን፣ ዓ/ነገሮችን ወዘተ የሚማረው ከአካባቢው ህብረተሰብ ነው ፡፡ ቋንቋችን የሚለያየውም የሰውነት ክፍሎቻችን በመለያየታቸው ሳይሆን የአካባቢያችን ህብረተሰብ በሚኖረው ቋንቋ ሥርዓት መለያየት የተነሳ ነው ፡፡

በዚህ ላይ ልናነሳው የምንችለው ጉዳይ በየአካባቢያችን የተለያዩ ቋንቋዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ሌላ ከቋንቋ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጥያቄ ለቋንቋ መዳበር ወሳኝ የሚባል እድሜ አለ ወይ? የሚለው ነው። በዚህም ላይ በጠረጴዛችሁ ተወያዩበት!

ከላይ የተነሳነውን ጥያቄ ለመመለስ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቲት ቋንቋ እድሜ ሙሉ ሊያድግ ወይም ሊዳብር ቢችልም ወሳኝ የሚባለው እድሜ ግን የቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ ነው ፡፡ ለዚህም ዋቤ የሚያደርጉት አብዛኞቻችን በአምስት አመት እድሜ 90% የሚሆነውን የቋንቋ ዕድገት ላይ እንደርሳለን ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-**

**እስኪ በቤታችሁ /በሰፈራችሁ የሚገኙ የአምስት ዓመት ህፃናትን በዓይነ ህሊናችሁ ተመልከቱና የቋንቋ ዕድገታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለጓደኛችሁ ንገሩ፡፡**

በሦስተኛ ደረጃ ልንረዳው የሚገባ ነገር ደግሞ የቋንቋ ዕድገትና የቋንቋ መዳበር የሚሉትን ፅንሰ ሃሳቦች ነው፡፡ ከላይ እንደተመከታችሁት ለዚህ ስልጠና የተጠቀምንበት ርዕስ የቋንቋ መዳበር የሚለው ነው፡፡ ለምን ይመስላችኋል? በሁለቱት መካከል ያለውስ ልዩነትና አንድነት ምንድን ነው? እስኪ ተወያዩና ምላሻችሁን ንገሩን ፡፡

________________________________________

________________________________________

________________________________________

በጣም ጥሩ! ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው ደግሞ በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ ደረጃ ያሉ ህፃናት / ልጆች ቋንቋን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ ይሆናል፡፡

### 1.2. የቋንቋ መዳበር በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ

**የንዑስ ክፍሉ ትምህርት ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍል ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/ የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የቋንቋ መዳበር ጥቅምን ያብራራሉ፣
- በልጆች የቋንቋ መዳበር ሂደት የህብረተሰብ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ያብራራሉ።
- የልጆችን ቋንቋ ማዳበር የሚቻልበትን ሁኔታ ይገልጻሉ።

ቀ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የምንመለከታቸው ዋና ጥያቄዎች የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህፃናት ቋንቋ እንዴት ሊዳብር ይችላል? ማን እንዴት ሊረዳ ይችላል ? የሚሉትን ይሆናል፡፡

**ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች ፡-**

ሦስት፣ ሶስት በመሆን በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ የህፃናትን ቋንቋ ማዳበር ስለሚቻልበት ሁኔታና በዚህ ሂደት ተሳታፊ መሆን ስላለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎችና ድርሻቸው ተወያዩ ፡ ________________________________________

ከላይ በጠቀስነው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተሰጡ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ ቋንቋን እንዴት ማዳበር እንደሚቻልና ህፃናትን እንዴት ለትምህርት ዝግጁ ማድረግን እንደሚኖርብን እንመለከታለን ፡፡

ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች ፡-

ስለዝግጁነት በተደጋጋሚ የምናነሳው በቂ የቋንቋ መሠረት ያላቸው ህፃናት በትምህርታቸው ውጤታማ የመሆን እድላቸው ከሌሎች የተሻለ መሆኑን ጥናቶችና ተሞክሮዎች ስላረጋገጡ ነው ፡፡ ምክንያቱም ቋንቋቸው የዳበረ ህፃናት ከሌሎች ጋር የመግባባት፣ ሀሳብ የመለዋወጥ፣ የማሰብ፣ ችግር የመፍታት፣ በራስ የመተማመን ወዘተ ችሎታዎችን የተላበሱ ናቸው ፡፡ ይህም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በቀላሉ ለመቀላቀልና ለመግባባት፣ የትምህርቱን ሥራ ለመቀበል የተመቻቸ ዕድል ይፈጥርላቸዋል ፡፡ ስለዚህ ስለ ቋንቋ ዝግጁነት የምንነጋገረው ለትምህርት ሥራ ፍላጎትን የሚጨምር፣ መነቃቃትን የሚፈጥር ፣ በራስ መተማመንን የሚያጎለብት መሠረት ስለሆነ ነው ፡፡

ሌላ የምትጨምሩበት ካለ ________________________________________

የቋንቋ መሠረቱ የሚጣለው በእናቶችና ሞግዚቶች / አሳዳጊዎች ነው ፡፡ ከዚህም በላይ ቋንቋ የሚያብበው በእነዚህ ወገኖች ነው ፡፡ ይህም በጥናቶች ተረጋግጧል፡፡ ሰለዚህ እናቶች፣ ሞግዚቶችና ቤተሰብ ህጻናቱ በዚህ በትምህርት (ንባብና ፅሁፍ፣ ስሌት፣ ግንኙነት) በተገነባ ህብረተሰብ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ካስፈለገም ተወዳዳሪ ሆነው እዲወጡ ለማስቻል ቋንቋን በማዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በዚህ ረገድ እነዚህ

ወገኖች በሚገባ ተረድተው ሁኔታዎችን ካመቻቹና በቂ ጊዜ መስጠትን ጨምሮ ህጻናቱን ካበረታቱ ለህጻናቱ ቋንቋ መዳበር ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የተመቻቹላቸው ህጻናትም የቋንቋውን ድምፆች ፣ ቃላት፣ ዓ/ነገሮች ፣ በመረዳትና በመጠቀም ለቀጣይ የትምህርት ቤት ሥራዎች ዝግጁ ይሆናሉ፡፡ ትምህርት ቤት መግባትንም እንደ ጥሩ አጋጣሚ ይወዱታል፤ ትምህርቱንም በደስታ ይከታተላሉ፤ የተሻለ ውጤትም ያስመዘግባሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የእናንተ የመምህራን ድጋፍ ሲጨመርበት ይሆናል ማለትነው።

በነገራችን ላይ የቋንቋ የመጀመሪያው ምልክት ከእናት ማህፀን ስንወጣ የምናሰማው ድምፅ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ድምፅ ወደ አዲስና ያልተለመደ አካባቢ (ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ቦታ) መምጣትን በተፈጥሯዊ ስሜት /reflex/ በመረዳት መግለፅን ያመለክታሉ፡፡ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ቋንቋ እንማራለን ፡፡ እናት፣ሞግዚት/አሳዳጊ ቤተሰብም ለዚህ የመማር ሂደት መሠረቱን ይጥላሉ፡፡ በመቀጠልም ቤተሰብ፣ አካባቢና ህብረተሰብ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ወደ ቅድመ መደበኛ ትምህርት በመምጣት ሰፋ ካለ ህብረተሰብና ለየት ያለ ስርዓት በመለማመድ ለትምህርት / መደበኛ ለማለት ነው/ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

በቤተሰባችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ያሉ ህፃናትን በመውሰድ ቋንቋቸውን በማዳበር ሂደት የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች (ቤተሰብን ጨምሮ) የሚጫወቱን ሚናና ጥሩ ተሞክሮአቸውን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡ ______________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________

በመቀጠል የቋንቋ መዳበርን የተመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችና ሂደቱን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን፡፡

### 1.3. የቋንቋ ግብዓቶችና ተከታታይነት ያለው ግንኙነት

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- በልጆች ቋንቋ መዳበር ሂደት ጠቃሚ ግብአቶችን ይለያሉ፣
- ለቋንቋ ክትትል ወሳኝነትን ያብራራሉ፣
- የቋንቋ መዳበር ሂደትን ያስረዳሉ፣

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የምንመልሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ህፃናት ቋንቋን ምን ያህል ይማራሉ?
2. በህፃናት ቋንቋ መማርና መዳበር ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱት እነማን ናቸው?
3. ቋንቋን መማር የሚጀመረው መቼ ነው ?

እስካሁን ካደረግነው ውይይትና ከራሳችሁም ልምድ በመነሳት ከላይ የተመለከትኩትን ጥያቄዎች ለአምስት ደቂቃ ተነጋገሩባቸውና የቡድን መልሳችሁን ስጡ፡፡

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ሰዎች ቋንቋን መማር የሚጀምሩት እንደተወለዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በድምፅ ፣ በፈገግታ፣ በሳቅ፣ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመጠቀም ስሜታቸውንና ሃሳባቸውን ይገልፃሉ፤ የሌሎችን ስሜትና ሁኔታም ይረዳሉ፡፡ የእናታቸውን ስሜትም ማንበብ ይችላሉ፡፡ የደስታ፣ የሃዘን ስሜትን ከፊት ላይ እንደማንበብ ማለት ነው፡፡

ለመሆኑ ቋንቋን ለመማር የሚጠቅሙን የሰውነት አካሎች የትኞቹ ናቸው? ለአንድ ደቂቃ ተነጋገሩበት ___________________________________________________

__________________________________________________________________

______________________________________________________

አዕምሮአችን የቋንቋ መዳበርን የተመለከተ ሥራ የሚከያከናውን ክፍል አለው ፡፡ የግራው የዐዕምሮአችን ክፍል ይህን ስራ ያከናውናል። ሌሎች አካሎቻችንም ጉሮሮ፣ ትናጋ፣

ምናስ፣ አፍንጫን ጨምሮ ለቋንቋ ትምህርት አስፈላጊ ናቸው ፡፡ እነዚህና ሌሎች የሰው ልጆች የሰውነት ክፍሎቻችን ከሌሎች እንስሳት በተለየ ቋንቋን በመጠቀም የላቀ መግባባትና መረዳት እንዲኖረን ረድተውናል ፡፡

በዚህ ላይ የምትጨምሩበት ወይም የምትቀንሱት አስተያየት ካለ ________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
__________________________________

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውን ተፈጥሮአዊ ፀጋዎች በመጠቀም ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት (ቤተሰብንና ትምህርት ቤትን ጨምሮ) ቋንቋን መማር እንችላለን ፡፡

ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡- ቋንቋን የመማር ሂደቱስ ምን ይመስላል ? እስኪ ተነጋገሩበት

______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________

ቋንቋን በተለይም የአፍ መፍቻ ቋንቋን የምንማረው ሌሎችን በመቅዳትና በሙከራ ሂደት ነው፡፡ ቋንቋን የምንማረው ስህተትን በማረምና በማስተካከል ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት መሳሳት፣ መቀላቀል፣ ወዘተ የተለመዱና የማይታለፉ ናቸው፡፡

እስቲ እናንተም ሆነ ቤተሰቡ ውስጥ የሚገኝ ሌላ ህፃን ቋንቋ የተማረበትን ሂደት በማስታወስ ለጓኛችሁ ንገሩ!

______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
___________________________________________________

በመቀጠል የወላጆችንና የሞግዚት/ አሳዳጊ ሚናን እንመለከታለን ፡፡ በቅድሚያ እስኪ በየጠረጴዛው ተወያዩበት፡፡

ወላጆችና ሞግዚቶች ለህፃናቱ ስሜትን የመረዳትንና የመግለፅን  ሁኔታ ያስተምራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሙቀት፣ ቅዝቃዜን፣ ጣዕምን፣ሃሳብን በድርጊትና በሰውነት እንቅስቃሴ መግለፅ፣ፍቅርን ፣ ጥላቻን ፣ ትዕዛዝ መስጠትንና መቀበልን ወዘተ.መግለፅን ያስተምራሉ፡፡

### 1.4. ወላጆችና የህፃናት ቋንቋ መዳበር

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- ለህጻናት ቋንቋ መዳበር እናቶች/አሳዳጊዎች የሚጫወቱትን ሚና ሂደት ይገልጻሉ፣፡
- እእናቶች/አሳዳጊዎች  የህጻናት ቋንቋን ለማዳበር የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ይለያሉ፣

ከእስካሁኑ ትምህርታችንና ውይይታችን ለህፃኑ/ኗ የመጀመሪያ የቋንቋ መምህር  ማን ነው ብትባሉ ወላጅ እንደምትሉ አልጠራጠርም ፡፡

ታዲያ ወላጆች የህፃትን  ቋንቋ መዳበር እንዴት ሊያፋጥኑት ወይም ሊያቀጭጩት ይችላሉ? በቤታችሁ ወይም በአካባያችሁ ያሉ ህጻናት ቤተሰብን በመውሰድ ወላጆች የሚሳድሩትን ተፅዕኖ ተነጋገሩበት ፡፡

ለአምስት ደቂቃ ተነጋገሩ!

የወላጆችንና የአሳዳጊዎችን ሚና በተመለከተ ጥናቶች የሚከተለውን አረጋግጠዋል፡፡

- እናቶች ከህፃናት ጋር ለመግባባት የሚጠቀሙባቸውንድምፆች፣ቃና ህፃናቱ የቋንቋውን ሥርዓት እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል፡፡
- የዓይን ለዓይን ግንኙነት፣ የፊት ገፅታ ንባብ ወ.ዘ.ተ ህፃናት ስሜትንና ቋንቋውን እንዲረዱ ያግዛል፡፡
- ህፃናት በሚመገቡበት ፣ በሚፀዳዱበት ፣ በሚጫወቱበት ሁኔታ ሁሉ ቋንቋውን ይማራሉ፡፡
- የወላጆችን ንግግር መከታተል ነገሮች/ድርጊቶች መጀመራቸውን፣መጠናቀቃቸውን፣ መቀጠላቸውን ለመረዳት ያስችላል፡፡
- መዝሙሮች የህፃናትን ቋንቋ ክህሎት ያዳብራሉ፣
- ህጻናት በተደጋጋሚ የሚሰሙአቸውን ቃላትና ድምፆችን ቀድመው ይረዳሉ፡፡ ቋንቋ የሚዳብረው እንደሌላው ትምህርት ሁሉ በድግግሞሽ ነውና ፡፡

ከዚህ ላይ የምትጨምሩበት ካለ ____________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

________________________________________________________

### *1.5 ቤተሰብ፤ ባህልና ቋንቋ*

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የቤተሰብ ባህልና ቋንቋ ለህጻናት ቋንቋ መዳበር ያላቸውን ሚና ይገልጻሉ፣፡
- ቤተሰብ የህጻኑ/ኗን ቋንቋ ለማዳበር ሊተገብሯቸው የሚገቡ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣
- ቤተሰብ የህጻኑ/ኗን ቋንቋ ለማዳበር የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች ይለያሉ፣

በዚሁ ንዑስ ርዕስ ሥር የምንመለከተው ቤተሰብና ባህል ቋንቋን ምን ያህል እንደሚቀርፁ ይሆናል ፡፡

ወደ ጥናት ግኝቶች ከማለፋችን በፊት በአካባቢያችን ቤተሰብና ባህል በቋንቋ ዕድገት መዳበር ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ እንመለከት፤ እንወያይ፡፡

ለውይይታችን እንዲያመች የምታውቁትን ቤተሰብና ባህል ውሰዱ፡፡

በመቀጠል ጥናቶች ከላይ ያነሳነውን ጉዳይ በተመለከተ የዘገቡትን እንመለከታለን፡፡ ወላጆችና አሳዳጊዎች / ሞግዚቶች የመጀመሪያው የቋንቋ ትምህርት መምህራን እንደመሆናቸው የሚከተሉትን ሚና ይጫወታሉ፡፡

- መረጃንና መመሪያን ማዳመጥ፣
- ተሞክሮአቸውን (ያዩትንና የሰሙትን) ማደራጀትና መግለፅ፣
- ችግሮችን መፍታትና መተንበይ ፣
- ጥያቄ መጠየቅና መመለስ፣
- በውይይት ወቅት የውይይቱን ደንብና ሥርዓት ተከትሎ መሳተፍ ፤
- ጠቃሚ ታሪኮች በጥሞና ማዳመጥ ወዘተ ናቸው።

ሌላ የምትጨምሩት ካለ፡-

በዚህ ሂደት ወላጅና ሞግዚት /አሳዳጊ/ ሊያውቋቸውና ሊተገብሯቸው የሚገቡ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የሚጠቀሙባቸው ቃላት ከህፃኑ/ኗ ተሞክሮና ከስሜት አካላት ተግባራት /ማየት፣ መስማት፣ መንካት፣ መቅመስ፣ ማሽተት/ ጋር ማያያዝ፣
- የሚሰጡት አስተያየትና የሚጠቀሙባቸው ቃላት ከህፃኑ/ኗ ገጠመኝ ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ጥያቄዎች ድግግሞሽን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማመቻቸት ምሳሌ፡- ይህ ምንድን ነው? ቀለሙስ? ከሌላኛው በምን ይለያል? ወ.ዘ.ተ
- ጥያቄዎች እንዲያስቡና እንዲያገናዝቡ የሚረዱ ይሁኑ፡፡ ምሳሌ ቀይ ነገር አሳየ/ይኝ! ሌላ መፈለግ ትችላለህ? ሞክርና ንገረኝ! እዚህ ቤት/ክፍል ውስጥ ፈልግ/ጊ ወ.ዘ.ተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

**ውድ ሰልጣኞች/ የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-**

ከላይ ያነሳናቸው ሃሳቦች በቅድመ መደበኛ ትምህርት የቋንቋ መዳበር ሂደት ያላቸውን አንድነትና ልዩነት በመመልከት እናጠቃልል፡፡

በአምስት ደቂቃ የማጠቃለያ ሃሳባችሁን አቅርቡ!

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________

1.6የቋንቋ መዳበርና የሪሶርስ እጥረት

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- ለህፃናት ቋንቋ መዳበር አስፈላጊ ሪሶርሶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ለህፃናት ቋንቋ መዳበር የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደረጃ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ያብራራሉ፡፡
- ለህፃናቱ የቋንቋ መዳበር ወላጆች፣ሞግዚቶችና መምህራን ሊጫወቱ የሚችሉትን ሚና ይዘረዝራሉ፡፡

መጀመሪያ የሪሶርስ እጥረት ስንል ምን ማለታችን ነው? እጥረቱንስ እንዴት ልንወጣው እንችላለን? እንዴት?

______________________________________________

______________________________________________

___________________________________

ጥናቶች እንዳረጋገጡት ተነሳሽነት ያላቸው ወላጆች የሪሶርስ እጥረትን በመቅረፍ የህፃናትን ቋንቋ ማዳበር ይችላሉ፡፡ እንዴት ቢሉ ጊዜና ትኩረት በመስጠት ነው መልሱ፡፡ ለህፃናት በቂ ጊዜና ትኩረት የማይሰጡ ወላጆች የህፃናቱን ቋንቋ ማዳበር በአሉታዊ መልኩ ተፅዕኖ ያሳድሩበታል፡፡ የቃላት ብዛት፣ የዓረፍተ ነገር አጠቃቀም፣ ማዳመጥ፣ ችግር መፍታት፣ የመግባባት ችሎታ ማነስ እንደምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ይህ ችግርም በትምህርት ቤትና በትምህርት አቀባበል ሂደት ይንፀባረቃል፡፡ ለመምህራኑም ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል፡፡ መምህራኑም ህጻናቱ ከዚህ ችግር የሚላቀቁበትን መንገድ መፈለግ ይኖርባቸዋል። ዝርዝሩን ወደፊት እናያለን፡፡

ለአንድ ደቂቃ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ አስቡ! ____________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

ከሪሶርስ እጥረት ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደረጃ ነው፡፡ ይህም ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍል ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ አመዳደብ የገቢ፣ የሥራ፣ የማህበራዊ ብሎም የትምህርት ደረጃን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መደብ የህፃኑ/ኗን ግንኙነት ይወስናል፡፡ ይህ ግንኙነትም የቋንቋ መዳበር ሂደትን ይወስናል፡፡

ለመሆኑ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደረጃ መለያየት በቋንቋ መዳበር ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ነው የሚያሳድረው? የትኛው ደረጃ ላይ ያሉት ላይ ነው አሉታዊ ተፅዕኖ የሚኖረው? ህፃናቱን ለመርዳትስ ምን መደረግ አለበት? ለአምስት ደቂቃ ተወያዩበት፡፡

አቅርቡ!

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

____________________________________________________________

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከከፍተኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚመጡ ህፃናት የቋንቋ መዳበር ደረጃቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ከዝቅተኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚመጡ ህጻናትም እነደዚሁ ናቸው።ይህም የሚሆነው ከሌሎች (እኩዮቻቸውን ጨምሮ) የመገናኘትና የመጫወት፣ ሃሳብ የመለዋወጥ ፣መፍትሄ የመፈለግ አጋጣሚያቸው ውሱን በመሆኑ ነው፡፡

ለማጠቃለል ለህፀኑ/ኗ የቋንቋ መዳበር ወላጆች፣ አሳዳጊዎች/ሞግዚቶችና መምህራን ሊጫወቱ የሚችሉትን ሚና አጠር አድርገን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

**ወላጆች፡-** ለልጆቻቸው በቂ ጊዜ መስጠት፣ በተለያዩና በሚመጥናቸው ጉዳዮች ላይ ማወያየት (ምሳሌ ነገሮች እንዴት እንደሚሠሩ፣ እንደሚገናኙ፣ እንደሚለያዩ)፣ ማረሚያና ማስተካከያ መስጠት፣ ተሞክሮአቸውን ማካፈል፣ ተረቶችንና ታሪኮችን፣ እንቆቅልሾችን መንገርና እነሱንም ማዳመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች እኩዮቻቸው ጋር እንዲገናኙ፣ እንዲጫወቱና ችግሮችን መፍታት እንዲለምዱ መፍቀድና ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

**ሞግዚቶች/አሣዳጊዎች፡-** ህፃናት የነገሮችን ሂደት፣ አሠራር፣ ግንኙነትና ልዩነት፣ የተለመዱና አዲስ እንግዳ ነገሮችን እንዲገልጹ፣ የተለያዩ አማራጭ ቃላትን እንዲጠቀሙ፣ ገጠመኞቻቸውን እንዲናገሩ መርዳት ያስፈልጋል።

**መምህራን፡-** የህፃናቱን ድምፆችና ቃላት ትኩረት መስጠት፣ ከመልመዳቸው በመነሳት ነገሮችን ማገናኘት፣ ሂደቶችን በቅደም ተከተል ማቅረብ፣ ማበረታታትና ማሞገስ ወ.ዘ.ተ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

እናንተ የምትጨምሩት ካለ፡-

________________________________________________________________

________________________________________________________________

__________________________________________________

## 1.7 ህፃናትን ለትምህርት ቤት ማዘጋጀት

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናትን ቋንቋ ለመደበኛ ትምህርት ብቁ/ዝግጁ የሚያደርጉባቸውን ዘዴዎች ይለያሉ፣
- ህጻናቱን ፦ ለመደበኛው ትምህርት ብቁ/ዝግጁያ ደርጋሉ፣

ወደ ዝርዝር ይዘቱ ከመግባታችን በፊት ቅድመ መደበኛና መደበኛ ትምህርት ትርጉማቸውን፡ አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን እናያለን፡፡ እነዚህን ፅንሰ ሃሳቦች ካሁን በፊት በወሰዳችኋቸው የስልጠና ርዕሶች (የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፔዳጎጂና የልጆች አስተዳደግ) በስፋት ተመልክታችኋቸዋል፡

ማን ይነግረኛል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_________________________________________________________

በአጭሩ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህፃናትን ለመደበኛው ትምህርት ዝግጁ ማድረግ ስንልስ ምን ማለታችን ነው? ለምንስ አስፈለገ? እንዴትስ ዝግጁ እናደርጋቸዋለን? ዝግጁ የምናደርግባቸው መስኮችስ ምን ምን ናቸው? የማዘጋጀቱ ሥራስ በዋነኛነት የማን ነው?

በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ለአስር ደቂቃ ተወያዩ! በአንድ ቡድን ውስጥ ከሦስት እስከ አምስት አባላት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_________________________________________

መልካም! የቋንቋ ዝግጁነት ያለው/ላት ህፃን ቋንቋውን ተጠቅሞ/ማ መግባባትን፣ ሃሳብ መግለጽን፣ የሌሎችን ሃሳብ መረዳትን፣ ነገሮችን ማገናዘብን፣ ደንብና ሥርዓትን መረዳትና መጠበቅን፣ ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስን ወ.ዘ.ተ በቀላሉ ሊያከናውን/ልታከናውን ይችላል/ትችላለች፡፡ ይህ ዝግጅትም ትምህርት ቤትንና ጓደኞቻቸውን ለመናፈቅ፣ የትምህርት ሥራውንም ለመወደድ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ወላጆችና የቅድመ መደበኛ ትምህርት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራን ህፃናቱን ዝግጁ ማድረግ ለመደበኛ ትምህርቱም የመሠረት ድንጋይ ማኖር ይሆናል፡፡

ይህ ዝግጅት ከሌላቸው ህፃናቱ መደበኛ ትምህርት ቤት ለመሄድ ይጠላሉ፡፡ ለትምህርቱ ሥራ ትኩረትና ፍቅር ሊያጡ ይችላሉ፡፡ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡ በትምህርታቸውም ውጤታማ ያለመሆን እድላቸው ሰፊ ይሆናል፡፡ ይህንን አሉታዊ ተጽዕኖ ነገር ለማስወገድ ወላጆች (በአካባቢያችሁ የሚገኙ ማለታችን ነው) ምን ያድርጉ ትላላችሁ?

ተወያዩበትና ምላሽ ስጡን፡-

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

__________________________________________

እናንተ ከዚህ በላይ የጠቀሳችኋቸው ሀሳቦች እንዳሉ ሆነው ወላጆች የሚከተሉትን በማከናወን ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

- የህፃናት መፃህፍትን በመጠቀም ለህፃናቱ ቋንቋ መዳበር እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ታሪኮችን ማዳመጥ፣ ሥዕሎችን መመልከት ሊረዳ ይችላል፣
- ድምፆችን፣ ታሪኮችን፣ መዝሙሮችን እንዲያዳምጡ ማድረግ፣
- እንቆቅልሾችን በመፍታት የችግር መፍታትንና የቋንቋ ክህሎታቸውን ስለሚያዳብሩ አካባቢያዊ ነገሮችንና ሂደቶችን በመጠቀም እንቆቅልሾችን መናገር፣ ማዳመጥ፣
- የህፃናቱን ድርጊት/ተግባር በቃላት መግለጽ፣
- የሂደቶችን ቅደም ተከተል በቃላት መግለጽ፣

**ምሣሌ፡-**

- የመመገብ ሂደት ቅደም ተከተል
- የመኝታ ዝግጅት ቅደም ተከተል ወ.ዘ.ተ ሊሆን ይችላል፣፤

ሌላ በአካባቢያችሁ ተሞክሮ ካለ ግለፁልን፡፡ ________________________________

______________________________________________________________________

__________________________________________________________

### *1.8 ቋንቋና የህፃናት ጨዋታ*

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- ጨዋታ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ ዋና ተግባር መሆኑን ይረዳሉ፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ከጨዋታ ጋር ያለውን ትስስርና ጥቅም ያብራራሉ፣
- ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናት ጨዋታንያመቻቻቻሉ፣
- ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናት ትምህርትን በጨዋታ መልክ ያቀርባሉ፣

**ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ ህፃናት ዋና ሥራ ምን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? ከልጆች አስተዳደግ ሥልጠና ላይ የምታስታውሱት ይመስለኛል፡፡ ዋና ሥራቸው ጨዋታ ነው፡፡ ለዚህም ነው ይህ እድሜ የጨዋታ እድሜ የሚባለው።

ለመሆኑ ህጻናት ለምን ይጫወታሉ? በምን ይጫወታሉ? ጨዋታ ለምን ይጠቅማቸዋል?

| |
|---|
| እስኪ በዚህ እድሜ ክልል ያሉ ህፃናትን በመውሰድ ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡_______________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________ |

በአጭሩ ለማስቀመጥ፣ ህፃናት በየትኛውም ቦታ፤ ጊዜ፣ እቃ፤ ጨዋታን ይፈጥራሉ፣ ይጫወታሉ፡፡ በዚህ ሂደትም የቋንቋ ችሎታቸው ይዳብራል፡፡ አዕምሮአቸው ይሰፋል፣ አካላቸው ይጠነክራል፣ ግንኙነታቸው ይሰፋል፤ ይሰምራል፤ ወ.ዘ.ተ ስለዚህ ጨዋታ የዕድገትና የመዳበር መንገዳቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሚጫወቱበትን ሁኔታና እድገታቸውን ማመቻቸት ነው፡፡ ስለዚህ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ያስፈልጋል።፡

የተለያዩ ጨዋታዎችን (ምሳሌ፣ ሌሎችን በማስመሰል/በመኮረጅ ፣ በድራማ መልክ ወዘተ.) ማከናወን ይቻላል። ሌላ የምትጨምሩበት ካለ ጥቀሱ! በአካበቢያችሁ የሚገኙ ህፃናት ጨዋታና የቋንቋ መዳበርን ወደ ኋላ ዞር ብላችሁ ተመልከቱ ፡፡

| |
|---|
| የራሳችሁን ልምድም ልታካትቱ ትችላላችሁ፡፡ ______________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________ |

### 1.9. የንባብ ዝግጁነት ቋንቋ የሚያጫውተው ሚና

| |
|---|
| **የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡** |
| የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡- |

- ጨዋታ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ ዋና ተግባር መሆኑን ይረዳሉ፣
- የ መደበኛ ትምህርት ከጨዋታ ጋር ያለውን ትስስርና ጥቅም ያብራራሉ፣
- የቋንቋ መዳበር ለንባብ ዝግጁነት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ይገልጻሉ፤፡
- ወላጆችና መምህራን ለህጻናቱ የንባብ ዝግጁነት የሚከተሉትን መንገድ ይዘረዝራሉ፣

ወደ ዝርዝር ጉዳዩይከመግባታችን በፊት የቋንቋ መዳበር ለንባብ ዝግጁነት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ እንመለከታለን፡፡ የወላጆች ሚና ምን ይሆናል ?

ተወያዩበት!

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ወላጆች በሚከተሉት መልኮች የልጆችን ንባብ ሊያጎለብቱ ይችላሉ፡፡

1. የህፃናት መፅሐፍትን መግዛት፣ በየዕለቱ ታሪኮችን ማንበብ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ ወዘተ፣
2. ህፃናት ፊደላትን እንዲያነቡ ፣ ሥዕሎችን እንዲስሉና ታሪኮችን ለወላጆች እንዲነግሩ ማድረግ፣
3. የህፃናት ግጥሞችን ማንበብ ፣ የቃላት ጨዋታን ማጫወት ፣
4. ከባህሉና ከአካባቢው የተገኙ ታሪኮችን መንገር፣
5. የሥዕል መፅሀፍትን በመጠቀም ታሪኩን እንዲረዱ ማድረግ፣
6. የእናንተ የመምህራን ሚናስ? እስኪ ለአንድ ደቂቃ ተወያዩበት፤፤

### 1.10 ቋንቋና ማህበራዊ ተግባቦት

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የማህበራዊ ተግባቦት ለቋንቋ መዳበር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ያብራራሉ፣

- ለማህበራዊ ተግባቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፣

**ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች**

ቋንቋ ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ የመግባቢያ መሳሪያ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልከተናል ፡፡ ይህንን መሳሪያ የተመለከቱ አጠቃላይ ጉዳዮች ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ይህንን መሳሪያ በመጠቀም ነው ሃሳባቸውን ፣ ልምዳቸውን ፣ ዕውቀታቸውን፣ ስሜታቸውን የሚጋሩት ፣ አካባቢያቸውንም የሚፈትሹት የሚረዱትና የሚለውጡት፡፡ ችግሮቻቸውንም የሚፈቱት ፡፡

ይህ መሳሪያ ባይኖረን ኖሮ የሰው ልጆች ህይወት ምን ልትመስል እንደምትችል አስባችሁ ታውቃላችሁ

እስኪ አስቡና ንገሩን ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________

ይህንን መሳሪያ በህፃናት ለማዳበር ከእኛ ከወላጆችና ከመምህራን ምን ይጠበቃል ?

አምስት ደቂቃ ውሰዱና ተነጋገሩ !______________________________________

______________________________________________

______________________________________________

## 1.11 ቋንቋና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች

**የንኡስ ክፍል-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- የቋንቋ መዳበር ለሌሎች ትምህርቶች የሚፈጥረውን ዝግጁነት ይረዳሉ፣
- የህጻናቱን ቋንቋ በማዳበር ለመደበኛው ትምህርት ዝገጁ ያደርጋሉ፣

ውድ ሰልጣኞች ከዚህ ርዕስ የተረዳችሁት ፍሬ ሃሳብ ምንድ ነው? ______________________
______________________________________________________________________________
_________________________________________________________________________

የዚህ ርዕስ ዋና ጭብጥ / መልዕክት ቋንቋ ሌሎች ትምህርቶችንም ያግዛል፣ ለብዙዎችም መሳሪያቸው ነው ፡፡ መጀመሪያውንም ቋንቋ የሰው ልጆች መግባቢያ መሳሪያ ነው ብለናል፡፡

የየዕለት ገጠመኞቻችንን ፣ ልምዳችንን፣ ስሜታችንን፣ የነገሮችንና ክስተቶችን ግንኙነቶች እንገልፅበታለን። ምሳሌ፡- መጠን ፣ ብዛት፣ ጥራት፣ ቅርፅ፣ ቀለም ፣ አቅጣጫ፣ ጊዜ ፣ ቦታ ፣ ቅደም ተከተል እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ። በመሆኑም ሙዚቃንም ሆነ ሂሳብን ፣ ሳይንስንም ሆነ ሥነ ውበትን ለመማር / ለማጥናት ቋንቋን እንጠቀማለን ፡፡

ሌላ የምትጨምሩበት ካለ ______________________________________________________
______________________________________________________________________________
_________________________________________________________________________

ከዚህ በኋላ የመጀመሪያውን ምዕራፍ እናጠናቅቃለን ፡፡ ከሦስት - አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የምዕራፉን ማጠቃለያ ፍሬ ሃሳቦችን ዘርዝሩ፣

ተንትኑም ! ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

### 1.12 የምዕራፉ ማጠቃለያ

የሚከተሉት ሀሳቦች የምዕራፉ ማጠቃለያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. ቋንቋ ለሰው ልጅ መግባቢያ የተሰጠ መሳያሪ ነው ፡፡ ይህንን መሳሪያ በመጠቀም ሀሳቡን፣ ኑሮውን ፣ ዕውቀቱን ፣ ልምዱን ፣ ደስታውን ይገልፃል፣ ይግባባል፡፡
2. ወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመጀመሪያ መምህራን ናቸው ፡፡ የቋንቋውን ፣ ፣የቋንቋውን ድምፆች ፣ ቃላትን፣ ዓ/ነገሮችን ፣ ትርጉምን ያስተምራሉ ፡፡
3. ወላጆች፤ አሳዳጊዎች / ሞግዚቶች የህፃናቱን የቋንቋ መዳበር ሊያጎለብቱ ወይም ሊያኮስሱ ይችላሉ፡፡ በቂ ተሞክሮ መስጠት ፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
4. ቋንቋ የሌሎች ትምህርቶች መማሪያ መሳሪያም ነው ፡፡ የፈጠራ መሳሪያም ሆኖ ያገለግላል፡፡ ስለዚህ የህፃናት ቋንቋ ከመሠረቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
5. መምህራንም ሕፃናትን ቋንቋ በማዳበር በኩል የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በቀጣይ የምናየውም ይህንን ይሆናል ።

ትንሽ ማነቃቂያ

እንቆቅልሽ (2)

ምን አውቅልህ አትሉም?

እሽ።

እማ ሲሉ ይነካኩ

አባ ሲሉ ይነካኩ

አያ ሲሉ አይነካኩ፤እወቁልኝ፤፤

መልሱን በአባሪ 5 ተመልከቱ።

በድጋሚ አመሰግናሁ፡፡

የምዕራፉ የሙከራ ጥያቄዎች

ክፍል1፡- እየእውነት ሀሰት ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች በማንበብ ትክክለኛ ለሆነው «እውነትእ» ላልሆነው ደግሞ «ሀሰት» በማለት ለመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ ላይ መልሱ።

___1. መግባቢያ ሁሉ ቋንቋ ነው::

___2. የሰዎች ቋንቋ የሚለያየው በውርስ/ዘር /Heredity/ ስለተገኘ ነው::

___3. ቀንቋ በጨዋታ ሊዳብር ይችላል።

___4. የቋንቋ ችሎታ/ዝግጁነት ለሂሣብ ትምህርት ጠቃሚ ነው::

___5. የመጀመሪያው የቋንቋ መምህር ቤተሰብ ነው::

ክፍል 2: የምርጫ ጥያቄዎች

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመልስ መስጫ ቦታው ላይ ጻፉ::

___6. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ የቋንቋ ወሳኝ እዕድሜ ነው::

ለ) ብዙውን ጊዜ ቴሌቭዥንን ከሚከታተል ህጻን ይልቅ ከወላጆቹ ጋር የሚወያይ ህጻን የተሻለ የቋንቋ ዝግጁነት ይኖረዋል።

ሐ) የወላጆች ቋንቋ የልጆቻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይሆን ይችላል::

መ) መልሱ አልተሰጠም::

___7. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ቋንቋ የፈጠራ መሣሪያ ሊሆን ይችላል::

ለ) የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህፃናት ማንበብና መፃፍ መቻል ይጠበቅባቸዋል::

ሐ) ህፃናት ከጨዋታ ይልቅ ቁም ነገር ላይ ማተኮር አለባቸው::

መ) ከተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቤተሰብ የመጡ ህፃናት ከሌሎች የተሻለ የቋንቋ ችሎታ አላቸው::

___8. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ቋንቋ በተናገሪው ህብረተሰብ የሚታወቅ ሥርዓት አለው::

ለ) ቋንቋና አዕምሮ ግንኙነት የላቸውም::

ሐ) ቋንቋቸው የዳበረ ህፃናት ከሌሎች የተሻለ በራስ መተማመን ሊኖራቸው ይችላል።

መ) ህፃናት ቋንቋ መማር የሚጀምሩት እንደተወለዱ ነው።

___9. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ቋንቋ የሚዳብረው በመለማመድ ነው።

ለ) አጭር መልስ ያላቸው ጥያቄዎች ቋንቋን ለማስተማር ይመረጣሉ።

ሐ) ህፃናት ከመናገር ይልቅ ቢያዳምጡ የተሻለ የቋንቋ መዳበር ይኖራቸዋል።

መ) የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ዓላማ ለህፃናቱ ፊደላትንና ቃላትን ማስተማር ነው።

___10. የሚከተሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች የህፃናትን ቋንቋ ከማዳበር አንፃር የሚጫወቱትን ሚና መሠረት በማድረግ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።

ሀ) እናት -- አባት -- ቤተሰብ - -ሞግዚት -- መምህር

ለ) አባት -- እእናት -- ሞግዚት -- ቤተሰብ -- መምህር

ሐ) ሞግዚት -- እናት -- አባት--- መምህር -- ቤተሰብ

መ) መምህር --- እእናት -- አባት -- ቤተሰብ -- ሞግዚት

## ክፍል 3: አጭር መልስ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በግርጌ በተሰጠው ቦታ ጻፉ።

1. የአማርኛ ፊደላትን በሙሉ ቅርፃቸውንና መስመራቸውን በመጠበቅ ጻፉ።
2. የእንግሊዝኛ ፊደላትን /Capital እና□“ Small/ ቅርፃቸውንና ፊደላቸውን በመጠበቅ ጻፉ።

| መልስ መስጫ ቦታ |
| --- |
| |

| |
|---|
| መልሳችሁን ከሰጣችሁ በኋላ አባሪ 3ን ተመልክታችሁ  አርሙ። |

## 2.  በቅድመ-መደበኛ ትምህርት  የቋንቋ ዝግጁነትን እንዴት ማምጣት እንችላለን?

**የንኡስ ክፍለ-ትምህርቱ ዓላማ/ግብ፡**

የዚህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የማዳመጥ ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የንግግር  ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎችን ይገነዘባሉ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የንግግር  ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎችን ይገነዘባሉ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የንባብ  ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎችን A[ÇK<፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት የጽሁፍ  ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎችን ይለያሉ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናት ለመደበኛው ትምህርት የቋንቋ ዝግጁነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፣

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው እኛ መምህራን  የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናት ቋንቋቸውን እንዲያዳብሩ ለመርዳትና ለመደበኛ  ትምህርት ዝግጁ ለማድረግ የምንከተላቸውን ዘዴዎች ይሆናል። ይህም አራቱን የቋንቋ  ክህሎቶች (ማለትም ማዳመጥ፤ መናገር፤ ማንበብና መፃፍ) እንዲሁም በእያንዳንዳቸው ስር ዘርዝር ያሉ ክህሎቶችን ከዚህ እደሚለከተለው እንመለከታለን።

1) የማዳመጥ ክህሎት ማዳበር
   - 1.1. ሌሎችን ማዳመጥ መቻል መቻል
   - 1.2. የሰሙትን ድምጽ አስመስሎ ማውጣትና መለየት መቻል
   - 1.3. መዝሙሮችን፣ ተረቶችን፣ ገጠመኞችን፣ ማድመጥ መቻል
2) የንግግር ክህሎት ማዳበር
   - 2.1. ተቀባይነት ባለው መልኩ ራስን መግለጽ መቻል
   - 2.2. ስላዩትና ስለሰሙት ነገር በዝርዝር መናገር መቻል
   - 2.3. በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ምንነት፣ ባህሪ፣ ቀለም፣ መጠን መናገር

መቻል

2.4. ተረቶችን፣ መዝሙሮችን መልሶ መናገር፤ በድራማ ማንፀባረቅ መቻል

2.5. ለጥያቄዎች በተሟላ ዓ/ነገር መልስ መስጠት መቻል

2.6. ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች በማየት ታታሪክን መናገር መቻል

3) ለንባብ ዝግጁ መሆን

3.1. ዕቃዎችን በቀለም፣በቅርጽ፣ በመጠን መመደብ መቻል

3.2. ስዕሎችን በማየትና በማወዳደር ልዩነትን መናገር መቻል

3.3. መሪ ፊደላትን በድምጽና በቅርጽ መለየትና ማንበብን መለማመድ

3.4. ስዕሎችንና ፊደላትን ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ ማንበብን መለማመድ

3.5. የስዕልና የተረት መጽሐፍ በሥርዓት መያዝና ገፆችን መግለጽ መቻል

4) ለጽሁፍ ዝግጁ መሆን

4.1. ስዕሎችንና በድርብ የተጻፉ ፊደላትን ከመስመር ሳይወጡ ቀለም (Color) መቀባትን መለማመድ

4.2. የተለያዩ መሰረታዊ  መስመሮችን መሥራት መቻል

4.3. ስዕሎችን፣ ቅርፆችንና ፊደሎችን መስመር ጠብቆ ማድመቅ መቻል

4.4. በተለያዩ ነገሮች አስመስሎ መሥራትና መፃፍን መለማመድ

4.5. የዓይን፣ የአእምሮና  የእጅ ቅንጅትን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል

ህፃናቱን በነዚህ ዝርዝር ክህሎቶች ዝግጁ ለማድረግ እንዲቻልም መድረሻ/ግብና መለኪያዎች፣ የመርጃ መሳሪያዎች፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ዘዴዎች ጥቆማ ይደረጋል።

አሁን የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ህጻናት ቋንቋቸውን በማዳበር እንዴት ዝግጁ እንደምናደርግ እናያለን፤ በ4 ቡድንም እንከፈላለን፤ ቁጥር በመጥራት ከ 1 እስከ 4 ቡድናችንን  እንለያለን፤ በቁጥራችን መሰረት እንደራጃለን፤ እያንዳንዱ ቡድንም በአንድ ክህሎት ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል፤ ከዚህ በታችበቀረበው መልኩ የሚከናወን ይሆናል ማለት ነው።

በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የቋንቋ ዝግጁነትን እንዴት ማምጣት እንችላለን?

1. በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የማዳመጥ ዝግጁነትን እንዴት እናዳብር?

የመጀመሪያው ቡድን የማዳመጥ ክህሎትን እንዴት እንደምናስተምር ሰርቶ ያቀርብልናል።

የትኩረት ነጥቦቹም፡-

- ሌሎችን ማዳመጥ
- ድምፆችን መለየት
- መዝሙሮችን፣ ታሪኮችን፣ ተሞክሮዎችን፣ ወዘተ
- መድረሻ ግብና መለኪያ
- መርጃ መሳሪያ
- የመስተማሪያ ዘዴ ይሆናሉ።

2. በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የንግግር ዝግጁነትን እንዴት እናዳብር?

የሁለተኛው ቡድን የንግግር ክህሎትን እንዴት እንደምናስተምር ሰርቶ ያቀርብልናል

የትኩረት ነጥቦቹም

- ራስን መግለጽ
- ያዩትንና የሰሙትን ሪፖርት ማድረግ
- ንግግርን በድራማ፣በትረካ፣በመዝሙር መግለጽ
- ጥያቄቆችን በተሟላ ዐ/ነገር መመለስ
- ስዕሎችንና ታሪኮችን መንገር
- መድረሻ፣ ግብና መለኪያ
- መርጃ መሳሪያ
- የማስተማሪያ ዘዴ ይሆናሉ።

3. በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የንባብ ዝግጁነትን እንዴት እናዳብር?

የሶስተኛው ቡድን የንግግር ክህሎትን እንዴት እንደምናስተምር ሰርቶ ያቀርብልናል።

የትኩረት ነጥቦቹም፡-

- ራስን መግለጽ
- ያዩትንና የሰሙትን ሪፖርት ማድረግ
- ንግግርን በድራማ፣በትረካ፣በመዝሙር መግለጽ
- ጥያቄዎችን በተሟላ ዐ/ነገር መመለስ
- ስዕሎችንና ታሪኮችን መንገር
- መድረሻ፣ ግብና መለኪያ
- መርጃ መሳሪያ

- የማስተማሪያ ዘዴ ይሆናሉ።

4. በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የፅሁፍ ዝግጁነትን እንዴት እናዳብር?

የአራተኛው ቡድን የፅሁፍ ዝግጁነትን እንዴት እንደምናዳብር ሰርቶ ያቀርብልናል። የትኩረት ነጥቦቹም

- ፊደላትንና ስዕሎችን ቀለም መቀባት
- ፊደላትን፤ ስዕሎችንና ቅርፆችን ማድመቅ
- አስመስሎ መፃፍና መቀባት
- እጅና ዐዕምሮን አቀናጅቶ መፃፍ
- መድረሻ፤ ግብና መለኪያ
- መርጃ መሳሪያ
- የማስተማሪያ ዘዴ ይሆናሉ።

የቡድን ስራው ሂደትና አቀራረብ የሚከተለውን ይመስላል። የቡድን ስራው በ15 ደቂቃ ይከናወናል።

- አቀራረቡ በቅደም ተከተል ይሆናል፤
- ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ 10 ደቂቃ ይሆናል
- ጥያቄዎች
- አስተያየት
- ምላሽና ማብራሪያ
- ጠቅላላ አስተያየት ይሰጣል ።

አሁን ደግሞ ትንሽ ማነቃቂያ፡-

እንቆቅልሽ (3)

ምን አውቅልህ አትሉም?

እሽ፤፤

ቀይ ሙሽራ

በነጭ አጥር ታጥራ፤ እወቁልኝ፤፤ (መልሱን በአባሪ 5 ተመልከት/ች፡፡)

ሌላ ኢነርጃይዘር ያለው ካለ

እናመሰግናለን፡፡

ቀጥሎ በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የቋንቋን ዝግጁነትን እንዴት ማምጣት እንችላለን? የሚለውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የቀረቡ ምላሾችን በጋራ እናያለን።

## 1. የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎት ማዳበርን እንመለከታለን። የመድረሻ ግብና መለኪያ መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማር ዘዴዎች ተካተዋል::

**1.1. መድረሻ/ግብ**: የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ**፤ ሌሎችን ማዳመጥ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ለሕፃናት በየግላቸው ትዕዛዞችን መስጠትና ዘዙሉ መሠረት ማከናወናቸውን በመከታተል ማበረ ታታትና የማዳመጥ ዝንባሌአቸውን ማዳበር
- በዜና ክፍለ ጊዜ /በተለይ ሰኞ ቀን/ ቅዳሜና እሁድ የዕረፍት ቀናትን እንዴት እንዳሳለፉ መናገርናእያንዳንዳቸው እ እንዲናገሩ በማድረግ ማበረታታት ጓደኞቻቸው እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ተረትን በማዳመጥ ክፍለ ጊዜ የየራሳቸውን ተረትእን ዲናገሩ ማድረግና ሌሎች እንዲያዳምጡ ማበረታታት
- እእርስ በእርሳቸው ቀላል ትዕዞቸችን እ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣ ሲተገብሩ መከታተልና ማዳመጣቸውን ማረጋገጥ
- የተለያዩ ሐሳቦችን በአጭር ነገር፣ በሹክሹክታ በጆሮ መናገርና ያዳመጡትን አጠገባቸው ላሉት ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ በማድረግ የሹክሹክታ ጨዋታን ማጫወት

**የመርጃ መሣሪያዎች:-** የተረት መጽሐፍት

**1.2. መድረሻ/ግብ**፤ የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ**: የሰሙትን ድምጽ መለየትና አስመስሎ ማውጣትን መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በግቢ ውስጥ/በክፍል ውስጥ ለተወሰነ ሰከንድ ፀጥ ብለው እንዲያዳምጡ ማድረግ በፀጥታታ ውስጥ ምን እንዳዳመጡ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

- የተለያዩ እእንስሳት /የውሻ፣ የድመት ወዘተ. . ./ ድምጽን እንዲሰሙ በማድረግ የሰሙትን ድምጽ አስመስለው እንዲያወጡ ማድረግ፣ ከተሳሳቱ ደጋግመው እንዲሞክሩ በማበረታታት ማለማመድ
- የፊሽካ፣ የከበሮና ሌሎች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚሰሟቸውን ድምፆች ማሰማትና ቁሳቁሶችን ወይም ስዕሎችን በመደርደር የየትኛው ቁሳቁስ ድምጽእ እንደሆነ ለይተውእንዲያወጡ በማድረግ ማዳመጥን ማለማመድ
- «ማን ነው የጠራህ» ጨዋታን ለማጫወት አንድ ሕፃን ፊቱን አዙሮ እእንዲቆም ማድረግና አንድ ሌላ ሕፃን በመቕቆም እንዲጠራው ማድረግ «ማነው የጠራህ» ብሎ በመጠየቅ ማዳመጥን፣ ድምጽ መለየትን ማለማመድ

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** የእንስሳት ስዕል፣ ፊሽካ፣ ከበሮ፣ ድምጽ የሚሰጥ
የመጫወቻ መኪና

**1.3. መድረሻ/ግብ፤** የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ፤** መዝሙሮች ተረቶችን ገጠመኞችን ማድመጥ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በቴፕ የተቀረፀ መዝሙሮችእ እንዲያዳምጡ ማድረግና ያዳመጡትን መዝሙር መልሰው እእንዲዘምሩ ማድረግ፣የመዝሙሩን ይዘት በመጠየቅ ማወያየት፣ በትክክል ካላዳመጡ በድጋሚ ማስደመጥና ባዳመጡት መሠረት እእንዲዘምሩ ማለማመድ
- የሕፃናት መዝሙርን በመዘመር እእንዲያዳምጡ ማድረግ በይዘቶቹ ላይ ማወያየት መልሰው እንዲዘምሩ በማድረግ ማዳመጥን ማበረታታት

- አጫጭር ከሕፃናት ሕይወት ጋር የተያያዙ ገጠመኞችን ማውራት፣ በጥሞና እእንዲያዳምጡ ማድረግና የየራሳቸውን ገጠመኞች እእንዲናገሩ በማበረታታት ርስበርስ መደማመጥን ማበረታታት
- ተረትን መተረክ ፣በጥሞና እእንዲያዳምጡ ማድረግ፣ ያዳመጡትን ተረት ምንነት ባሉታ ታሪኮቹን እ እነማን እ እንደሆኑ ፣ የትኛው የተረቱ ክፍል እንዳስደታቸው መጠየቅና ማወያየት፣ ደግሞ መተረትና ያዳመጡትን መልሰው እእንዲናገሩ ማደረግ

**የመርጃ መሳሪያዎች፡-** መዝሙርን የሚደግፉ መሣሪያዎች፣ በካሴት የተቀረፀ
መዝሙሮች፣ቴፕ፣ የተረት መጽሐፍ፣ተረቱን የሚደግፉ ስዕሎች

## 2. የንግግር ክህሉትን ማዳበር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የቅድመ መደበኛ ተማሪዎችን የንግግር ክህሎት ማዳበርን እንመለከታለን። የመድረሻ ግብና መለኪያ፣መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማር ዘዴዎች ተካተው ቀርበዋል።

2.1. **መድረሻ/ግብ፡** የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ፤** ተቀባይነት ባለው መልኩ ራስን መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ስለራሳቸው እንዲናገሩ ለማነቃቃት መጀመሪያ የራስን ስም፣ የመኖሪያ አድራሻን መናገርና እያንዳንዳቸውእስለራሳቸው በተሟላ አረፍተ ነገርና አድማጭ ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ እንዲናገሩ ማበረታታት፣ የተፈለገውን አቅጣጫ ይዘው ካልተናገሩ በጥያቄዎች መምራት፣ ሲናገሩ ጣትን አፍ ውስጥ መክቶት፣ እጅን ማፋተግ፣ማቀርቀር ወዘተ. . . ካለ ተፈላጊ ያልሆነ ባህሪ መሆኑን ህጻናቱ እንዲረዱና ድርጊቱን እንዲተውእ በተለያየ መንገድ መርዳት፣
- አሻንጉሊትን እንግዳ አስመስሎ ማምጣት፣ አሻንጉሊቷ /ስሟን ጠርቶ/ዛሬ ጠዋት ከቤታቸው ሲመጡ አዝነው ከሆነ፣ ደስ ብሎአቸው ከሆነ፣ ምን ዓይነት ስሜት እንዳላቸው እንዲነግሩኝ ነው ብላ የምትናገር በማስመሰል መናገርና በየተራ ወደ ሕፃናቱ አሻንጉሊቷን ይዞ በመቅረብ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለጥያቄው በንግግር መልስ ሲሰጡ ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት፣ማገዝ፣ በተገቢዉ ሥነ ሥርዓት እእንዲናገሩም መርዳት፣
- ተረትን በመጠቀም የወደፊት ፍላጎቱ ምን እንደሆነ ስለተናገረ ሕፃን በአጭሩ መተረክና እየእያንዳንዳቸው ሲያድጉ ምን መሆን እእንደሚፈልጉ በጓደኞቻቸው ፊት እእንዲናገሩ ማበረታታት፣

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** አሻንጉሊት፣ ለተረት ድጋፍ የሚሆን ስዕል

2.2. **መድረሻ/ግብ**፡- የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ**፡- ስላዩትና ስለሰሙት ነገር በዝርዝር መናገር መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በዕረፍት ቀናቸው ስላዩትና ስለሰሙት ለመናገር እንዲነቃቁ በመጀመሪያ መናገር፣ በመቀጠልም እእያንዳንዳቸው እንዲናገሩ ዕድል መስጠት፣ ማበረታታት፣ በዝርዝር መናገር እንዲችሉ ጥያቄዎችን ማቅረብና ማበረታታት፣ መናገር የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር በዝርዝር እንዲናገሩ ማድረግ፣

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** ስዕሎች መጽሔቶች

2.3. **መድረሻ/ግብ**፡- የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ**፤ ተረቶችንና መዝሙሮችን መልሶ መናገር፣ በድራማ ማንፀባረቅ  መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በአካባቢያቸው ጉብኝትን ማዘጋጀትና ከጉብኝት በኋላ ስላዩትና ስለሰሙት ነገር እንዲናገሩ ማበረታታት፣ ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲያስተውሉ ማገዝ፣ አገላብጠው ሊያዩት የሚችሉት ጎላ ያለ ስዕል ያለባቸውን መጽሔቶች/መጻሕፍት/መስጠት፣ በጥሞና አገላብጠውእ እንዲያዩ ጊዜ መስጠትና እያንዳንዳቸው አገላብጠው ስላዩት ስዕል እንዲናገሩ ማድረግ ።

**የመርጃ መሣሪያ፡-** ሕፃናትን ሊጎዱ የማይችሉ ትናንሽ ቁሳቁሶች፣ ለቶዎች፣ስዕሎች

2.4. **መድረሻ/ግብ**፡- የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ**፤ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን መጠሪያ፣ አገልግሎትና ባህሪ መናገር መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች፡-**

- ሕፃናት በክብ እንዲቀመጡ ማድረግ፣ በተቀመጡበት ቦታታ ሆነው እእጃቸውን ወደኋላ እንዲዘረጉ ማድረግና በእጆቻቸው ላይ የተለያዩ ነገሮችን ለምሣሌ ላጲስ፣መቅረጫ፣ ስኒ ወዘተ. ማስቀመጥና በመጀመሪያእ ሳያዩ  እየዳሰሱ በእጃቸው ላይ ስለተቀመጠው ነገር  እንዲናገሩ በመቀጠልም በአይናቸው እያዩትን እንዲናገሩ በማድረግ «በእጅህ ላይ ምን አለ?» ጨዋታን ማጫወት ።

- የእንስሳት፣የቤት ቁሳቁስ፣ የእጽዋት ሎቶን፣እእንዲገጣጥሙ በማድረግ ስለገጣጠሙት ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፣
- በዕለት ተዕለት የሚጠቀሙባቸውን ዕቃዎች በስዕል፣ ከተቻለም ቁሳቁሱን በማቅረብ እንዲመለከቱ በማድረግ መጠሪያ ስሙን፣ አገልግሎቱንና ባህሪውን እእንዲናገሩ ማበረታታት፣ተመሣሣይ ዕቃዎች ሆነው የተሠሩባቸው ማቴሪያሎች የተለያዮ የሆኑትን አስተውለው በማየት ልዩነታቸውን እእንዲያወጡ ማነቃቃት፣ /ለምሣሌ የብረትና የፕላስቲክ ማንኪያ፣ብርሃን የሚያስተላልፍና የማያስተላልፍ ብርጭቆና ኩባያ ወዘተ. . .ሊሆኑ ይችላሉ።

***የመርጃ መሣሪያ፡-*** ሕፃናትን ሊጎዱ የማይችሉ ትናንሽ ቁሳቁሶች፣ ለቶዎች፣ስዕሎች

2.5. ***መድረሻ/ግብ፡-*** የንግግር ክህሎትን ማዳበር

***መለኪያ፤*** ተረቶችንና መዝሙሮችን መልሶ መናገር፣ በድራማ ማንፀባረቅ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ለዕድሜያቸው የሚመጥን ተረትን ረጋ ብሎ መተረክ፣ በመቀጠልም ስለተረቱ የተሰማቸውን ስሜት እእንዲናገሩ ማድረግ፣ የተረቱን ይዘት እእንዲረዱ በቅደም ተከተል መጠየቅ፣ በመጨረሻም ተረቱን መልሰው እ እንዲተርኩ ዕድሉን መስጠት፣ ከከበዳቸው በጥያቄና መልስ መልክ ዕገዛ ማድረግ

- በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት ገፀ ባህሪያት ተላብሰው በድራማ መልክ እእንዲተውኑት ማድረግ

- አጫጭር የሕፃናት መዝመሮችን ስንኝ በስንኝ በመከፋፈል ማስጠናት፣ እእንዲዘምሩ ማድረግ፣ የመዝሙሩን ይዘት በጥያቄና መልስ በማወያየት እእንዲረዱ ማድረግ፣ በቡድን በመከፋፈል እንዲዘምሩ ማድረግና በቃላቸው እእንዲይዙት ደጋግሞ ማዘመር።

***የመርጃ መሣሪያዎች፡-*** የተረት መጽሐፍ፣ መዝሙሮችን አጃቢ ድምጽ የሚሰጡ ነገሮች /ማራካሽ፣ማጨብጨቢያ ወዘተ. . ./

**2. 5. መድረሻ/ግብ፡-** የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ፡-** ለጥያቄዎች በተሟላ ዓረፍተነገር መለስ መስጠት መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ህፃናቱን ስለራሳቸው የተለያዩ ቀላል ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተሟላና ትርጉም ሊሰጥ የሚችል ዐረፍተ ነገር በመጠቀም መልስእእንዲሰጡ ማበረታታት
- ተከታታይ ይዘት ያላቸውን ስዕሎች በመጠቀም በስዕሉ ላይ ስለሚታየው ነገር እንዲነግሩ መጠየቅና በተቻለ መጠን ተከታታይነቱን ጠብቀው ታሪኩን እንዲናገሩ ማለማመድ፣
- ሕፃናት በዕለት ተዕለት ህይወታቸው እ እነሱም ሆኑ አዋቂዎች የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች በአካልም ሆነ በስዕል በማሳየት መጠሪያ ስሙንና ግልጋሎቱን በመጠየቅ በተሟላ ዐረፍተ ነገር መልስ እእንዲሰጡ ማበረታታት

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** ስዕሎች፣ቁሳቁሶች

2.6. **መድረሻ/ግብ፡-** የንግግር ክህሎትን ማዳበር

**መለኪያ፡-**-ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን በማየት ታታሪክን መናገር፣ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች፡-**

ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች አዘበራርቆ በመስጠት ህፃናት በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡና ለምን እንደዚህ እእንዳስቀመጡ እንዲናገሩ በማድረግ ማበረታታት፣ በስዕል የተደገፉ የተረት መጽሀፎችን ገጽ በገጽ አገላብጠው ስዕሉን በማየት ታሪኩን እንዲናገሩ ማበረታታት፣ተረቱን ከዚህ በፊት የተዋወቁት ሊሆን ፡፡

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** የተለያየ ቀለም ያላቸው ቁሳቁሶች፣የጂኦሜትሪ ትርፆች፣የተለያየ መጠን ያላቸው የእንጨት ሽመሎች

## 3. የንባብ ዝግጁነትን ማዳበር

በዚህ ንኡስ ርዕስ ሥር የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች ለንባብ ዝግጁ እንዲሆኑ ክህሎቻቸውን እእንዴት ማዳበር እእንደምንችል እእንመለከታለን፡፡

**የመድረሻ ግብና መለኪያው፣** መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎችም ተካትተዋል፡፡

3.1. **መድረሻ/ግብ፡- ለንባብ ዝግጁ መሆን**

**መለኪያ፤** ዕቃዎችን በቀለማቸው፤ በቅርፃቸውና በመጠናቸው መመደብ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- የተለያዬ ቀለም ያላቸው ቁሳቁሶች /መጫዎቻዎች/ ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ በመስጠት በቀለማቸው እንዲመድቡ ማድረግና ቁሳቁሶቹን /መጫዎቻዎቹን/ ለምን በአንድ ላይ ሊመድቡአቸው እንደቻሉ እንዲገልጹ ማድረግ፣
- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን በመስጠት በየቅርጻቸው እንዲመድቡ ማድረግና ለምን በመደቡበት መንገድ ሊመድቡ እንደቻሉ እንዲናገሩ ማድረግ፣
- «ማን ቀድሞ ይመድባል?» የሚለውን ጨዋታ  በዚህ መልኩ በማጫወት ማጠናከር ይቻላል:: ፈቃደኛ የሆኑ ሁለት ሕፃናትን በመጋበዝ እኩል መጠን ያላቸውን በቀለማቸው ወይም በቅርፃቸው ወይም በቁመታቸው የተለያዩ የሆኑትን ቁሳቁሶች በሁለት ጠረጴዛ ላይ በማድረግ «ጀምር» የሚል ምልክት ሲሰሙ በታዘዙት መሠረት እእንዲመድቡ ማድረግ፣ የሌላውን ሥራ የተመለከተ ከጨዋታው ውጪ እንደሚሆንና ቀድሞ የጨረሰ «ጨረስኩ» ማለት እእንዳለበት ማስረዳት፣
- የጨዋታውን ሕግና ሂደት በመንገርአ እንዲረዱ ማድረግ፣ ቀድሞ የጨረሰውን ልጅ እንዲጨበጨብለት በማድረግ ማበረታታት፣ተሸናፊው ተጫዋችም በሌላ ጊዜ እሱ ማሸነፍ እንደሚችል በመንገር ለሁለቱም በማስጨብጨብ  በዚህ ዓይነት መንገድ ሁሉም ሕፃናት በጨዋታው ተሳታፊ እንዱሆኑ ማድረግ ::

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** የተለያየ ቀለም ያላቸው ቁሳቁሶች፣የጂኦሜትሪ ትርዖች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው የእንጨት ሽመሎች

**መለኪያ፤** ስዕሎችን በማየትና በማወዳደር ልዩነቱን መናገር መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች፣**

- ሁለት ተመሣሣይ የሆኑ ነገር ግን ትንሽ ልዩነት ያላቸውን ስዕሎች ለሕፃናቱ ዕይታታ አመቺ ቦታ ላይ በማድረግ ስዕሎቹንአ እንዲመለከቱና ምንአ እንደሆኑ

እእንዲናገሩ ማድረግ፣በሁለቱ ስዕሎች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲናገሩ ማበረታታት፣ከከበዳቸው ፍንጭ በመስጠት ልዩነቱን እንዲናገሩ ማድረግ፣

- በየጠረጴዛው ላይ ሶስት ሶስት ስዕሎችን በመስጠት /ሁለቱ የሚመሳሰሉና አንዱ ትንሽ የተለየ መሆን ይኖርበታል/ የትኞቹ ተመሣሣይ እንደሆኑና የትኛው የተለየ እንደሆነና በምን እንደተለየ እእንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት፣

- ለእያንዳንዱ ሕፃን ሁለት ተመሣሣይ የሆኑ ስዕሎችን በመስጠት በደንብ እእንዲመለከቱ ማድረግ፣ ከዚያም እየእያንዳንዱ ሕፃን እእየተነሳ የደረሰው ስዕል ምን እንደሆነና ልዩነቱ ምን እንደሆነ ንዲናገር ማበረታታት፣

ለምሣሌ፡- ሁለት እ እኩል ቁመትና ያታታ ያላቸውን የሕፃናት ስዕል በማየት «አንዱ ኮፍያ አድርጓል ፣ሌላው አላደረገም» በማለት መልስ እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል።

***የመርጃ መሣሪያዎች፡-*** የተለያዩ ብዕሎች

**3.3. *መድረሻ/ግብ፡-*** ለንባብ ዝግጁ መሆን

***መለኪያ፡-*** መሪ ፊደላትን በድምጽና በቅርጽ መለየትና ማንበብን ማለማመድ

**የማስተማር ዘዴዎች**

ሶስት በቅርፃቸው ተመሣሣይ የሆኑ የፊደል ሰሌዳዎችን በመምረጥ ሕፃናትን መተዋወቅ እእንደሚፈልጉ በማስመሰል መጠሪያ ስማቸውንና ቅርፃቸውን ለሕፃናቱ በመንገር ማስተዋወቅ ፣«ማን ነኝ» «ማን ነኝ?» የሚለውን መዝሙር በማዘመር ማጠናከር፣እእያንዳንዱ የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም እንዳለው እ እንዲገነዘቡ ማድረግ፣ የአሸዋ ግርፍ ፊደል ሰሌዳን /በብርጭቆ ወረቀት የተሠራ ፊደልን/ በመጠቀም ሕፃናቱ እእንዲዳስሷቸውና ስማቸውን እእንዲናገሩ ማድረግ ይቻላል።

- ለሕፃናቱ በፊደላቱ ስምና ቅርጽ ላይ የተመረኮዘ አጭር ተረትን በማዘጋጀት መተረክ፤ የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ ትንሽ መንደር ውስጥ የምትኖር «በ» የምትባል ባለ ሁለት እእግር ፊደል ነበረች፡፡ ይቺ ፊደል እእንደ እ እሷ ሁለት እግር ያለውና አብሯት የሚጫወት ፊደል ባለመኖሩ ብቸኛ ነበረች፡፡ አንድ ቀን ለምን እኔን የሚመስልና አብሮኝ

የሚጫወት ጓደኛ አልፈልግም ብላ ከቤቷ ወጥታ ወደሌላ መንገድ ጉዞ ጀመረች። በመንገድ ላይ ስትሄድ ከርቀት አንድ ትልቅ ዛፍ ስር እእሷን የሚመስል ፊደል አየችና እእየሮጠች ወደዛፉ ሄደች:: ከዚያም እእሷን ለሚመስለው ፊደል ማን እንደሆነች ከየትና ለምን እንደመጣች በዝርዝር ነገረችው:: እሱም «ሰ» እእንደሚባል ከነገራት በኋላ «በ»ን አትኩሮ እእያየት በጣም የሚገርም ነው አንቺና እኔ በጣም እእንመሳሰላን፣ እእኔ ከአንቺ የምለየው ጭንቅላቴ ላይ ቁንጮ ስላለኝ ብቻ ነው አላት። ከዚያም በመቀጠል እ እህተ እእንዳለችው ነገራትና ድምፁን ከፍ አድርጎ «ሸ»እእያለ እ እህቱን ተጣራ «ሸ»ም ከምትጫወትበት ቦታ በመምጣት ከ «በ» ጋር ተዋወቀች። «በ» ም «ሸ»ን አንቺና ወንድምሽ በጣም ትመሳሰላላችሁ፣ ከወንድምሽ የምትለይው አንቺ ፀጉርሽ ላይ ሪቫን ስላለሽ ነው አለቻትና «በ»የ«ሸ»ን ሪቫን ስለወደደችውእ እባክሽ ሪቫንሽን በጣም ስለወደድኩት እ እስቲ እ እኔም ጭንቅላቴ ላይ ላድርገው ብላ «ሸ»ን ጠየቀቻት:: «ሸ»ም በጣም አዝናለሁ፣ የእኔ ሪቫን ከፀጉሬ ላይ መውለቅ አይችልም በማለት እ እንደማይወልቅ ነገረቻት። ከዚያም «በ» «ሰ» እ እና «ሸ» አንድ ላይ አባሮሽ፣ ድብብቆሽ፣ ሌባና ፖሊስ ከተጫወቱ በኋላ ሲመሽ «በ» በሌላ ቀን መጥታታአብራቸው እእንደምትጫወት ነግራቸው ደስ እያላት ወደቤቷ ተመለሰች::

ማሳሰቢያ፣ ለሕፃናት በፊደላት ስምና ቅርጽ ላይ የተመረኮዘ አጭር ተረት በሚዘጋጅበት ጊዜ ገፀ ባህሪያቱ ራሳቸው ፊደላቱ መሆን አለባቸው:: የተረቱ ይዘት የገፀባህርያቱ /የፊደላቱ/ ድምጽና ቅርጽ ላይ በማተኮር በስዕል ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል።

- እእንቆቅልሽን በመጠየቅ የፊደላቱን ድምጽና ቅርጽ እንዲለዩ ማድረግ

ለምሣሌ- እእንቆቅልሽ/ህ

- እእኔ ከፊደላት ዘሮች አንዱ ነኝ
- ሁለት እግር አለኝ
- የተደፋ ብርጭቆ እእመስላለሁ
- እኔ ማነኝ?

- «የጎደለውን ዕወቅ»በማጫወት የፊደል ሎቶን እ እንዲያዛምዱና የፊደል ፐዝልን እእንዲገጣጥሙ በማድረግ ማጠናከር

- «ልትወጣ ነው» «ልትወጣ ነው» የሚለውን ጨዋታታ በዚህ መልኩ በማጫወት ሕፃናቱ የተዋወቁትን ፊደላት ድምጽና ቅርጽ እንዲለዩ ማድረግ፣ መምህራን ለሁሉም ሕፃናት ከተዋወቋቸው ፊደላት 5x5 ሴ.ሜትር የሆነ አንድ አንድ በወፍራም ክላሰር /ካርቶን/ላይ የተፃፈ ፊደላትን መስጠት ይችላሉ።: መምህር ከሕፃናቱ ፊት በመጠቆም 15x17 ሴ.ሜትር የሆነ የፊደል ሰሌዳን /የተዋወቁትን ፊደል/ ከኋላ ደብቆ መያዝ፣ ከዚያም «ልትወጣ ነው ልትወጣ ነው» በማለት በያዙት ፊደል አንዱን ለሕፃናቱ ማሣየት፣ ሕፃናቱ መምህር የያዙትን አይነት ፊደል ከያዙ እንዲያወጡ ማድረግና የፊደሏን መጠሪያ ስም በመጠየቅ እእንዲናገሩ ማድረግ፣ የተሳሳተ ሕፃን ካለ ራሱ የያዘውንና መምህር የያዙትን ፊደል በማስተያየት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲናገር በማድረግ ማስተካከል / ማረም/

**የመርጃ መሣሪያዎች:-** የፊደል ሰሌዳ፣ የፊደላት ሎቶ፣ የፊደላት ፐዝል፣ በአሸዋ/በብርጭቆ ወረቀት የተሰሩ የፊደል ሰሌዳዎች፣በወፍራም ወረቀት ላይ የተፃፉ ፊደሎች

**3.4. መድረሻ/ግብ፤** ለንባብ ዝግጁ መሆን

**መለኪያ፤** ስዕሎችንና ፊደላትን ከላይ ወደታታች ከግራ ወደቀኝ በማየት ማንበብን ማለማመድ

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በትልቅ ወረቀት ላይ ጎላ ያሉናእ እኩል መጠን ያላቸውን 3 ወይም 4 የተለያዩ ስዕሎች ከላይ ወደታች / ከግራ ወደ ቀኝ መሳል፣ ከዚያም ለሕፃናቱ አመቺ የሆነ ቦታታላይ በማድረግ ስዕሎቹን በረዥም እእንጨት ከላይ ወደታች በመጠቆም የስዕሎቹን መጠሪያ ሕፃናቱን በመጠየቅ እእንዲናገሩ ማድረግ፣

- የተዋወቋቸውንም ፊደላት ከላይ ወደታች ከግራ ወደ ቀኝ/ በመፃፍ በተራ እእንዲናገሩ ማድረግ

- ለሕፃናት በወረቀት ላይ ከላይ ወደታችና ከግራ ወደቀኝ ስዕሎችንና የተዋወቋቸውን ፊደላት በመሳልና በመፃፍ መስጠት፣ ሕፃናት ወጥተው

በጓደኞቻቸው ፊት ስዕሎችን/ፊደሎችን ከላይ ወደታች/ ከግራ ወደቀኝ በማንበብ መጠሪያ ስማቸውን እእንዲናገሩ ማበረታታት፣

- ለሕፃናት የተዋወቋቸውን ፊደላት 5x5 ሴ.ሜትር በሆነ ወፍራም ክላሰር /ካርቶኒ/ ላይ በመፃፍ መስጠትና ፊደላትን እየገጣጠሙ ከግራ ወደቀኝ ማንበብን እእንዲለማመዱ ማበረታታት፣

- ተንቀሳቃሽ ፊደላትንና ሻሸ ቦርድን በመጠቀም ሕፃናቱ የተዋወቋቸውን ፊደላት ገጣጥመው ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ፣

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** የፊደል ሰሌዳ፣ ወረቀት፣ ማርከር /ከለሮች/፣ ተንቀሳቃሽ ፊደላት፣ ሻሸ ቦርድ

3.5. መድረሻ/ግብ፡- ለንባብ ዝግጁ መሆን

**መለኪያ፤** የስዕልና የተረት መጽሐፎችን በሥርዓት መያዝና ገፆችን በስርዓት መግለጽ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- የሕፃናት የስዕል/የተረት መጽሐፍን በግራ እጅ  በቀኝ እጅ ከታች ጠርዙን በመያዝ ከቀኝ ወደ ግራእ እንዴት መግለጽ እ እንደሚቻል በማሣየት መንገርና ሕፃናቱም እእየወጡ የመጽሐፍ አያያዝንና አገላለጽን እእንዲለማመዱ ማድረግ፣

- ለሕፃናት የተለያዩ ስዕል ያላቸው መጽሔቶችንናመጽሐፎችን በመስጠት የመጽሐፍ አያያዝንና አገላለጽን እእንዲለማመዱ ማድረግ፣
- መጽሐፎች በእርጥብ እ እጅ ከተያዙ፣ ምግብና ውሃ ከተንጠባጠበባቸው ሊበላሹ እእንደሚችሉ በተግባር በማሳየት እንዲረዱ ማድረግ፣

- በሕፃናት ተወዳጅ ከሆኑት የስዕልና የተረት መጽሐፎች ውስጥ ለሕፃናት ደብዳቤ እእንደተላከላቸው መንገርና ደብዳቤውን ከፖስታ ውስጥ አውጥቶ ማንበብ፣ መጽሐፎች በመገንጠላቸውና በመቀደዳቸው ምክንያት እንደታታመሙና መጽሐፎቹን ለማከም የሚረዱ መሣሪያዎችን አብረው እንደተላኩ በመንገር አውጥቶ ማሳየትና ሕፃናቱ መጽሐፎችን ለማከም ፈቃደኛ መሆናቸውን መጠየቅ፣ ከዚያም የተቀደዱትንና የተገነጠሉትን መጽሐፎች ከሕፃናቱ ጋር አብሮ ማከም፣

/መሸፈን፣መለበድ/ በመጨረሻም መጽሐፎቹ ሕክምና ከተደረገላቸው በኋላ እእንደተሻላቸውና ሕፃናቱን እ እንዳመሰገኗቸው በመንገር እእነሱም ሆኑ ሌሎች ሕፃናት /አዋቂዎች በደንብ እንዲይዟቸውና እንዳይገነጥሏቸው አደራ እ እንዳሉ በመንገር ማጠቃለል፡፡

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** የስዕልና የተረት መጽሐፎች፣ማጣበቂያ ኮላ፣መቀስ፣ ረቀት፣ መጽሔቶች

## 4. የፅሁፍ ዝግጁነትን ማዳበር

በዚህ ንኡስ ርዕስ ሥር የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች ለፅሁፍ ዝግጁእ እንዲሆኑ መርዳትን እእንመለከታለን፡፡

የመድረሻ ግብና መለኪያው፣መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎችም ቀርበዋል፡፡

4.1. መድረሻ/ግብ፡- ለፅሁፍ ዝግጁ መሆን

መለኪያ፡- ከመስመር ሳይወጡ ከለር መቀባትን መለማመድ

**የማስተማሪያ ዘዴዎች**

- ለሕፃናት ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕልን ከመስመር ሳይወጣእ እንዴት ከለር መቀባት እእንደሚቻል ማሳየት፣ በመቀጠልም ጎላ ያሉ ስዕሎችን በመስጠት ከመስመር ሳይወጡ እ እንዲቀቡ ማድረግና በመጨረሻም የምን ስዕል እንደሆነና ምን ዓይነት ከለርእ እንደቀቡት እንዲናገሩ ማበረታታትና የራሳቸውን ስራ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያስተያዩት ማድረግ፣
- የተዋወቋቸውን ፊደላት ጎላ አድርጎ በድርብ ጽፎ ለሕፃናት በመስጠት ከመስመር ሳይወጡ እ እንዲቀቡ ማድረግ፣ የተቀቡትን ፊደል መጠሪያ ስምና የተቀቡትን የከለር ዓይነት ምእ እንደሆነ ወጥተው በጓደኞቻቸው ፊት እንዲናገሩ ማድረግ፣ ሥራቸውን በክፍል ውስጥ ለዕይታ አመቺ በሆነ ቦታታ ስማቸውን በመፃፍ መለጠፍ፣

- ለእእያንዳንዱ ሕፃን ወረቀት በማጣጠፍ ትንሽ መጽሐፍን በማዘጋጀት መስጠትና የፈለጉትን ነገር እእንዲሰሩ ማድረግ፣ ሰርተው ሲጨርሱ ከመስመር ሳይወጡ የሳሉትን ስዕል የፈለጉትን ከለር እእንዲቀቡ በመስጠት የዓይንና የእጅ ቅንጅታቸው እንዲዳብር ማድረግ፣

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከለር

**4.2.. መድረሻ/ግብ፡-** ለጽሁፍ ዝግጁ መሆን

**መለኪያ፡-** የተለያዩ መሰረታዊ መስመሮችን መሥራት መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ለሕፃናቱ ዕይታ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ትልቅ ወረቀት በመለጠፍ ቋሚ፣ አግዳሚ፣ ሰያፍ፣ ቅንፍ፣ ዝግዛግ፣ ነጠብጣብ፣ የመሣሠሉትን መሰረታዊ መስመሮችን በመሥራት ሕፃናቱም በተሰጣቸው ወረቀት ላይ እእንዲሠሩ ማድረግ፣
- ሕፃናት መሰረታዊ መስመሮችን በማገጣጠም የተለያዩ ምስሎችን እ እንዴት እእንደሚሠሩ ማሣየትና ማለማመድ፣ ለምሣሌ መንገድ፣ መሠላል፣ መስቀል፣ ፀሐይ፣ዝናብ ወዘተ. . .ሊሆኑ ይችላሉ።

- መሰረታዊ መስመሮችን በአየር ላይ እየሠሩ ለሕፃናት ማሣየትና ያዩትን በመሥራት እንዲለማመዱ ማድረግ፣

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** እእርሳስ፣ማርከር

**4.3. መድረሻ/ግብ፡-** ለጽሁፍ ዝግጁ መሆን

**መለኪያ፡-** ስዕሎችን፣ ቅርፆችን፣ ፊደሎችን መስመር ጠብቆ ማድመቅ መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- በነጠብጣብ የተሰሩ ጎላ ያሉ ስዕሎችን ቤት፣ መኪና፣ አበባ የመሣሠሉትን ስዕሎች ለሕፃናት በመስጠት መስመሩን ጠብቀው ማድመቅንእ እንዲለማመዱ እእድሉን መስጠት፣ የሰሩትንም በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እእንዲያሣዩና ምን እእንደሆነ እእንዲናገሩ ማድረግ፣

- የተለያዮ የጂኦሜትሪ ቅርፃችን በነጠብጣብ መሳልና እእንዲያደምቁ ማድረግ

- የተዋወቋቸውን ፊደላት ጎላ አድርጎ በነጠብጣብ በመፃፍ ሕፃናቱ ነጠብጣቡን ተከትለው እእንዲያደምቁ ማድረግ፣ ያደመቁትን ፊደልም ወጥተው በጓደኞቻቸው ፊት ፊደሉን እያሳዩ «ማነኝ ማነኝ ልጆች እወቁኝ?» ብለው በመዘመር የክፍል ጓደኞቻቸውን እእንዲጠይቁ ማድረግ

**የመርጃ መሣሪያዎች:-** እእርሳስ፣ ወረቀት፣ ከለሮች ወ.ዘ.ተ.

**4.4. መድረሻ/ግብ:- ለፅሁፍ ዝግጁ መሆን**

**መለኪያ፤** ፊደላትን፣ ቅርፃችን፣ በተለያዩ ነገሮች አስመስሎ መሥራትንና መፃፍን መለማመድ

**የማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የዛፍ ፍሬዎችን፣ የክብሪት እንጨቶችን፣ ቆርኪዎችን በመጠቀም ሕፃናት የተዋወቋቸውን ፊደላት /ቅርፃች/ በየጠረጴዛቸው ላይ በመሄድ እእንዴትእእንደሚሠሩ ማሳየትና ለሕፃናቱም ዕድሉን በመስጠት እእንዲለማመዱ ማድረግ፣ የሠሩት ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማበረታታት

- የውሃ ቀለምን በመጠቀም ጠቋሚ ጣትን ቀለም ውስጥ እየነከሩ የተዋወቋቸውን ፊደላትና ቅርፃች በየተራ በየተራ በመፃፍ ማሣየት፣ በመቀጠልም ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው የውሃ ቀለምና ወረቀት በመስጠት አስመስለው መፃፍን እንዲለማመዱ ማድረግ

- በወረቀት ላይ ሕፃናት የተዋወቋቸውን ቅርፃች፣ፊደላት በመስራት፣ በመፃፍ ከስሩ አስመስለው እእንዲሠሩና እእንዲጽፉ እእድሉን በመስጠት እእንዲለማመዱ ማድረግ

**የመርጃ መሣሪያዎች:-** የዛፍ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ የክብሪት እንጨቶች፣የውሃ ቀለም፣ ወረቀት፣ እርሳስ

**4.5. መድረሻ/ግብ፡- ለጽሁፍ ዝግጁ መሆን**

**መለኪያ፡-** የዓይንና የእጅ ቅንጅትን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል

**የማስተማር ዘዴዎች**

- ወፍራም ክላሰር ላይ የተለያዩ ቅርፆችን በስሱ መሣልና አልፎ አልፎ በዱልዱም መርፌ በመብሳት የሱፍ ክርን በመጠቀምኝ እንዴት እእንደሚጠለፍ ማሣየት፣ በመቀጠልም ሕፃናቱ ባዩት መሠረት ክርን በቀዳዳ ውስጥ በማውጣትና በማግባት የጥልፍ ሥራንእ እንዲለማመዱ ማድረግ፣ የሰሩት ምንእ እንደሆነ በመጠየቅ እእንዲናገሩ ማበረታታት

- በወፍራም ክላሰር ላይ ሕፃናቱ የሚያውቁትን ነገር እንዲስሉ ማድረግ፣ ኳስ፣ቤት፣ ዶሮ ወዘተ. . . ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያም ስዕሉን ኮላ በመለቅለቅ የተለያዩ የእህል ዘሮችን፣ ላባዎችን፣ ጥጥ የመሣሠሉትን በመጠቀም መሙላትና ለሕፃናቱም ቀለል ያሉ ስዕሎችን በመስጠት ባዩት መሠረት እእንዲሠሩ ማድረግ

- የተዋወቋቸውን ፊደላት ጎላ አድርጎ በወረቀት ላይ በመፃፍ ሕፃናት ውስጡን ማጣበቂያ /ኮላ/ በመለቅለቅ በተለያዩ ባለቀለም ቁርጥራጭ ወረቀቶች እእንዲሞሏቸው ማድረግ፣ ከዚያም በክፍል ውስጥ ለዕይታታ አመቺ ቦታታ ላይ መለጠፍ

**የመርጃ መሣሪያዎች፡-** ወፍራም ክላሰር፣ዱልዱም መርፌ፣ የሱፍ ክሮች፣ የዶሮ ላባ፣የእህል ዘሮች፣ ጥጥ፣ ባለቀለም ቁርጥራጭ ወረቀቶች

ትንሽ ኢነርጃይዘር/ ማነቃቂያ ያስፈልጋል አይደል?

ማን ያምጣ?

እሺ።

እኔ አንድ እንቆቅልሽ ልጨምር?

እሺ።

እንቆቅልሽ (4)

እንቆቅልሽ

መሂዱን ሂጃለሁ

የወፍ ማሪያ ሆኛለሁ፤፤

መልሱን በአባሪ 5 ተመልከቱ።

ሌላ ኢነርጃይዘር/ማነቃቂያ ያለው ካለ በደስታ  እንቀበላለን፤፤

እናመሰግናለን።

## 2.5. የምዕራፉ ማጠቃለያ

**ውድ ሰልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች፡-**

በዚህ ምዕራፍ ስር የተመለከትናቸውን ፍሬ ሃሳቦች የተመለከቱ ቃላትን፣ዘረዝሩ!

በመቀጠልም የተዘረዘሩት ቃላት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህፃናት ቋንቋን ለማዳበር ያላቸውን ተግባራዊ ጠቀሜታ ከአጠገባችሁ ለሚገኝ/ትገኝ ጓደኛችሁሌላ ሰው አስረዱ። ታ

በዚህ መልኩ የሁለታችሁን ሃሳቦች/ሥራዎች ከተለዋወጣችሁ በኋላ በቀጣይ ሥራችሁ (ማለትም ቋንቋን ከማዳበር አንፃር) ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን በጋራ ምረጡ:: የመረጣችኋቸውን ሃሳቦችም ከአጠገባችሁ ለሚገኝ ሌላ ቡድን አስረዱ፣አስተያየታቸውንም ተቀበሉ:: የእናንተንም አስተያየት ለእነርሱ ስጡ:: በመጨረሻም ከዚህ በታች እንደማጠቃለያ የቀረቡትን ሀሣቦች ተመልከቱ፣ ከእናንተ ማጠቃለያ ጋርም አገናዝቧቸው።

የማጠቃለያ ነጥቦች ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የቀረቡት የሚከተሉት ናቸው::

1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የህፃናቱን የቋንቋ ክህሎት ሊያዳብሩና ህፃናቱን ዝግጁ ሊያደርጉ ይችላሉ::
2. የእያንዳንዱ የቋንቋ ክህሎት (ማለትም ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብና መፃፍ) የራሱ የሆነ ግብ፣ይዘት፣መለኪያ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመርጃ መሣሪያ አለው::
3. የማዳመጥ ዝግጁነትን ለማምጣት (ማለትም ሌሎችን ማድመጥን፣ድምፅን አስመስሎ ማውጣትና መለየትን ወዘተ) በመዝሙሮች፣በተረቶችና በገጠመኞች ማስተማር/ማዳበር ይቻላል::
4. የንባብ ዝግጁነትን ለማምጣት (ማለትም ዕቃዎችንና ፊደላትን መለየትና መመደብ መፅሀፍን በጥንቃቄ መያዝ ወዘተ.) ፊደላትን ፣ሥዕሎችን፣ የተረት መፅሀፍትን መጠቀም እንችላለን።
5. የጽሑፍ ዝግጁነትን ለማምጣት (ማለትም ቀለም መቀባትን፣መስመር መስራትን ፣ ማድመቅን፣ አስመስሎ መስራትን ወዘተ) እርሳስ፣ ወረቀት፣ ማርከር፣ የዛፍ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ክሮች፣ ላባዎች፣የእህል፣ዘሮች ወዘተ. መጠቀም እንችላለን።

6. የህፃናቱን የቋንቋ ዝግጁነት በዓመቱ መጀመሪያ፣ አጋማሽና መጨረሻ መገምገምና ዓላማው ግብ መምታቱን /ማለትም የህፃናቱን ዝግጁነት/መለካትና አስፈላጊ ሲሆንም ማስተካከል የሚኖርብንን ጉዳይ መረዳት እንችላለን።

## የቋንቋ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም……………………………………………………

የሕፃኑ ስም……………………………………… ዕድሜ....................ጾታታ…………

የመምህሩ ስም………………………………………ዓመተ ምህረት…………………

ስለ ህጻኑ ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር መዝግቡ።

ደረጃዎቹ:-

1) መሻሻል የሚያስፈልገው
2) የታለመው ግብ የተገኘበት
3) ከታለመው ግብ በላይ የተገኘበት

**ማሣሰቢያ**:- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| **የቋንቋ ክህሎት** | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመት መጀመሪያ | በዓመት አጋማሽ | በዓመት መጨረሻ |
| 1. የማዳመጥ ክህሎት ማዳበር | | | |
| 1.1. ሌለችን ማድመጥ መቻል | | | |
| 1.2. የሰሙትን ድምጽ አስመስሎ ማውጣትና መለየት መቻል | | | |
| 1.3. መዝሙሮችን፣ተረቶችን፣ገጠመኞችን ማድመጥ መቻል፣ | | | |
| 2. የንግግር ክህሎት ማዳበር | | | |
| 2.1. ተቀባይነት ባለው መልኩ ራስን መግለጽ መቻል | | | |
| 2.2. ስላዩትና ስለሰሙት ነገር በዝርዝር መናገር መቻል | | | |
| 2.3. በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን መጠሪያ ምንነት፣ባህሪ ፣ቀለም፣ መጠን መናገር መቻል | | | |
| 2.4. ተረቶችን፣መዝሙሮችን መልሶ መናገርና በድራማ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማንፀባረቅ መቻል | | | |
| 2.5. ለጥያቄዎች በተሟላ ዓረፍተነገር መልስ መስጠት መቻል | | | |
| 2.6. ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች በማየት ታሪኩን መናገር መቻል | | | |
| 3. ለንባብ ዝግጁ መሆን | | | |
| 3.1. ዕቃዎችን በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን ፣ መመደብ መቻል | | | |
| 3.2. ስዕሎችን በማየትና በማወዳደር ልዩነትን መናገር መቻል | | | |
| 3.3. መሪ ፊደላትን በድምጽና በቅርጽ መለየትና ማንበብ መለማመድ | | | |
| 3.4. ስዕሎችንና ፊደላትን ከላይ ወደታች፣ ከግራ ወደቀኝ በማየት ማንበብን መለማመድ | | | |
| 3.5. የስዕልና የተረት መጽሐፍትን በሥርዓት መያዝና ገፆችን መግለጽ መቻል | | | |
| 4. ለጽሁፍ ዝግጁነት<br>4.1. ስዕሎችንና በድርብ የተፃፉ ፊደላትን ከመስመር ሳይወጡ ከለር መቀባትን ማለመማድ | | | |
| 4.2. የተለያዩ መሰረታዊ መስመሮችን መሥራት መቻል | | | |
| 4.3. ስዕሎችን፣ ቅርፆችን፣ ፊደሎችን፣ መስመር ጠብቆ ማድመቅ መቻል | | | |
| 4.4. በተለያዩ ነገሮች አስመስሎ መስራትና መፃፍን መለማመድ | | | |
| 4.5. የዓይንና የእጅ ቅንጅቶችን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል | | | |

ከአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተወሰደ (2002ዓ.ም.)

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች**

**ክፍል 1: የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛ ለሆነው «**እውነት**» ላልሆነው ደግሞ «ሀሰት» በማለት በመልስ መስጫ ቦታ ላይ መልሱ።:

__________1. የፅሁፍ ክህሎት ከንባብ ክህሎት ይቀድማል::

__________2. በጨዋታታ ማዳመጥን ማስተማር ይቻላል::

__________3. በካሴት የተቀረፀ ድምፅ ካልተገኘ ማዳመጥን ለህፃናት ማስተማር አይቻልም::

__________4. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ሕፃናቱ ዐ/ነገርን መፃፍ ማስቻል አለባቸው::

__________5. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህፃናትን ቋንቋ ለማዳበር ሲባል መምህሩ/ርቷ የተረትን መፅሀፍት መጠቀም ግዴታ የለበ/ባትም::

**ክፍል 2: የምርጫ ጥያቄዎች**

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመልስ መስጫ ቦታው ላይ ጻፉ።

____6. ከሚከተሉት ዐ/ነገሮች ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ትዕዛዞችን በግል መስጠት የማዳመጥ ዝንባሌን አያዳብርም::

ለ) በሹክሹክታ መናገር ከማዳመጥ ይልቅ የንግግር ክህሎትን ያዳብራል::

ሐ) የተረት መፅሀፍት የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር አይጠቅሙም::

መ) ገጠመኞች የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር ይጠቅማሉ::

____7. ከሚከተሉት ዐ/ነገሮች ውስጥ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ) አሻንጉሊትን ተጠቅሞ የንግግር ክህሎትን ማዳበር አይቻልም::

ለ) ሥዕሎችና መፅሄቶች የንግግር ክህሎትን ማዳበር ይችላሉ::

ሐ) የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀት የንግግር ክህሎትን ለማዳበር ይጠቅማል::

መ) ብረትና ፕላስቲክ ማንኪያን በመጠቀም የንግግር ክህሎትን ማስተማር ይቻላል::

____8. ከሚከተሉት ዐ/ነገሮች ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) የቤት ቁሳቁሶች ንባብን ለማስተማር ይጠቅማሉ::

ለ) ሥዕሎች ንባብን ለማስተማር አይጠቅሙም::

ሐ) ተረቶች ንባብን ለማስተማር አይጠቅሙም::

መ) ዐ/ነገሮች ንባብን ለማስተማር ይጠቅሙናል::

**ክፍል 3: አጭር መልስ ጥያቄዎች**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭርና የተሟላ መልስ ቀጥሎ በተሰጠው ቦታ ላይ ጻፉ።

9. በቅድመ መደበኛ ትምህርት የህፃናቱን የፅሁፍ ዝግጁነት ለማምጣት የምንጠቀምባቸውን ዘዴዎች ዘርዝሩ።

10. በቅድመ መደበኛ ትምህርት የህፃናቱን የቋንቋ ዝግጁነት ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸውን የመለኪያ ዘዴዎችና አጠቃቀማቸውን ግለጹ።

**የመልስ መስጫ ቦታ**

መልሳችሁን ከሰጣችሁ በኋላ አባሪ 3ን በማየት መልሳችሁን አርሙ።

# ዋቤ መፅሐፍት

**የስልጠና ሞጁሉ በዋነኛነት ሶስት ምንጮችን በዋቤነት ወስዷል።**

John Lybolt and Catherine Gottfred's material entitled Promoting Pre-School Language produced by The International Academy of Education (IAE), available at http://wwwibe.unesco.org.

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ (2002). **ከ4 — 5 ዓመት እድሜ ክልል ላሉ ህፃናት የተዘጋጀ የህፃናት አስተዳደግና ትምህርት አጋዥ ፅሁፍ፤** ያልታተመ፤፤

አዘጋጁ በረጅም ጊዜ/ የስራ ዘመኑ ያነበባቸውና የተጠቀመባቸው ፅሁፎችና ያካበተው የማስተማር፤ ማሰልጠንና ምርምር ልምድ።

## አባሪ 1: Basic Facts about Language

1. **Language** is a form of communication-whether spoken, written, or signed-that is based on a system of symbols. Language consists of the words used by a community and the rules for varyiong and combining them.
2. **Human beings** including children need language to speak with others, listen to others, read, and write. Our language enables us to describe past events in detail and to plan for the future. Language lest us to pass down information from one generation to the next and create a rich cultural heritage.
3. **Language is highly ordered.** The organization involves five systems of rules: phonology, morphology, syntax, semantics, and pragmatics. When we say rules, we mean that language is orderly and the rules describe the weay language works.
4. **Phonology** is the sound system of language including the sounds that are used and how they ma be combined.
5. **Morphology** refers to the units of meaning involved in word formation.
6. **Syntax** involves the way words are combined to form acceptable phrases and sentences.
7. **Semantics** refers to the meaning of words and sentences.
8. **Pragmatics** involves the appropriate use of language in different contexts. They differ from culture to culture.

Please note that all these rules do not develop at a time.

## አባሪ 2: አካባቢያዊ ግንዛቤ

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ህጻናት አፍ መፍቻ ቋንቋ ምንድነው?
2. በአካባቢያችሁ ወላጆች፤ አሳዳጊዎችና ቤተሰብ የህጻናትን ቋንቋ ለማዳበር የሚጠቀሙበት ዘዴ ምንድነው? ደካማና ጠንካራ ጎኑን መዝግቡና ተንትኑ።
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን የህጻናትን ቋንቋ ለማዳበር የሚጠቀሙበት ዘዴ ምንድነው? ደካማና ጠንካራ ጎኑን መዝግቡና ተንትኑ።
4. ወላጆች፤ አሳዳጊዎችና ቤተሰብ የህጻናትን ቋንቋ ለማዳበር የሚጠቀሙበት ዘዴ ምንድነው? ደካማና ጠንካራ ጎኑን መዝግቡና ተንትኑ።
5. አካባቢያችሁ የህጻናትን ቋንቋ ለማዳበር ያለውን ምቹነት ገምግሙ ።ደካማና ጠንካራ ጎኑን መዝግቡና ተንትኑ።
6. ቋንቋና መግባባት ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ተንትኑ
7. በአካባቢያችሁ የህጻናትን ቋንቋ መዳበር የተመለከቱ ተረቶችና ምሳሌዎችን ሰብስቡ፤ ለቋንቋ መዳበር የሚያበረክቱትን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖዎች ገምግሙ፣ተንትኑ
8. የአካባቢያችሁ ህብረተሰብ የህጻናትን ቋንቋ ለማዳበር የሚጠቀምባቸውን ሪሶርሶች ዘርዝሩ፤ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ገምግሙ፤ ተንትኑ።
9. ለቋንቋ መዳበር መከታተያ የተቀመጠውን ቅፅ ገምግሙ። ካስፈለገም አሻሽሉና ከባልደረቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት፤ በመጨረሻም ከትምህርት ቤቱ ሀላፊ ጋር ተወያዩበት።

ESD

## አባሪ 3፡ የምእራፍ አንድ የሙከራ ጥያቄዎች መልስ

**የምእራፍ አንድ የሙከራ ጥያቄዎች መልሳችሁን ከዚህ በታች ከተሰጡት መልሶች ጋር አገናዝቡ።**

**ክፍል 1፡- እውነት ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

**ክፍል 2፡-የምርጫ ጥያቄዎች**

6. መ
7. ሀ
8. ለ
9. ሀ
10. ሀ

**ክፍል 3፤ አጭር መልስ ጥያቄዎች**

11. የፊደል ገበታን ተመልከቱ።

 አስፈላጊ ከሆነም ደጋግማችሁ ተለማመዱ።

**12.** CAPITAL LETTERS: A B C D E F G H I J K L M N O P Q R S T U V W X Y Z.

**Small letters: a b c d e f g h i j k l m n o p q r s t u v w x y z**

‘The quick brown fox jumps over the laze dog’ የሚለውን የእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር ደጋግማችሁ በመጻፍ ተለማመዱ።

ለማስታወስ ያህል የእንግሊዝኛ ፊደላት የተለያየ መስመር /ማለትም ከፊሎቹ ከመስመር በላይ ይወጣሉ፤ ከፊሎቹ ከመስመር በታች ይወርዳሉ፤ ከፊሎቹ ደግሞ መሀል መስመር ይይዛሉ።

## አባሪ 4፡ የምእራፍ ሁለት የሙከራ ጥያቄዎች መልስ

**የምእራፍ ሁለት የሙከራ ጥያቄዎች መልሳችሁን ከዚህ በታች ከተሰጡት መልሶች ጋር አገናዝቡ።**

**ክፍል 1፡-እውነት ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት
2. እውነት
3. ሀሰት
4. ሀሰት

**ክፍል 2፡- የምርጫ ጥያቄዎች**

5. ሐ
6. ሀ
7. ሀ

**ክፍል 3፤ አጭር መልስ ጥያቄዎች**

8. ገጽ 49 - 53 ተመልከቱ።

9. ገጽ 57-58 ተመልከቱ።

## አባሪ 5፡ የእንቆቅልሽ መልስ

እንቆቅልሽ 1፡ ሰዓት

እንቆቅልሽ 2፡ ከንፈሮች

እንቆቅልሽ 3፡ ምላሽ

እንቆቅልሽ 4፡ የቤት ምሰሶ

አንድ የሳይኮሎጂስቶች አባባል ልውሰድና ላጠቃል።

Early foundations are critical.

**የሰው መሰረቱ የልጅነት ዘመኑ ነው(ተብሎ ሊተረጎም ይችላል)።**